# የሀዲያ ህዝብ ታሪክ እና ባህል

አለባቸዉ ኬዕሚሶ
እና
ሳሙኤል ሀንዳሞ

ሀምሌ 2002 ዓ.ም

# የሀዲያ ህዝብ ታሪክ እና ባህል

©አለባቸዉ ኬዕሚሶ እና ሳሙኤል ሀንዳሞ፤ 2002፣
ሰፋር አታሚ፤አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ይህን መጽሀፍ በኤሌክትሮኒክስ እና/ወይም በሀትመት ሚዲያዎች ወይም በፎቶ ኮፒ መሳሪያዎች በከፊል ሆነ ሙሉ ለሙሉ ማባዛትና ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

የሽፋን ዲዛይን፤ ቴምድሮስ ብርሃኑ

## Hadiyya People: history and culture

Copyright©2010 by Alebachew Kemiso and Samuel Handamo

የመጀመሪያዉ እትም 2002 ዓ.ም

## ምስጋና

የዚህ ስራ ጥንስሱ አምስት አመታትን የኋሊት ይሄዳል፡፡ ጅማሬዉ በሀዲያ ታሪክና ባህል የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ ጥናታዊ ስራ በመስራትና በጥናቱ ዉጤቶች ላይ ወርክሾፕ በማካሄድ ነበር፡፡ ቀጥሎ መጽሀፉ ተዘጋጅቶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ተከታታይና ሰፊ መረጃ የማሰባሰብና የማጠናቀር ስራ ተሰርቷል፡፡

ለዚህ ስራ ግብ መቺነት አስተዋጽኦ ያደረጉት በርካታ ወገኖች ናቸዉ፡፡ በተለይ በሀዲያ ሴራ ላይ በተደረገዉ ጥናት ሰፊ መረጃ እንድናገኝ በአልያንስ ፎር ፒስ ኤንድ ዴቬሎፕሜንት በኩል የኖርዌይ ቤተ-ክርስቲያን ተራድኦ ስላደረገልን የገንዘብ ድጋፍ ምስጋናችን የላቀ ነዉ፡፡

ከዚህ ስራ ጅማሬ እስከ ፍጻሜ በማበረታታት፣ ጠቃሚ ሀሳብ በመስጠት፣ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሂደት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ከጎናችን የነበርከዉ አኔቦ ወልደጊዮርጊስ ያደረከዉ ትልቅ አስተዋጽኦ ምንጊዜም የማይዘነጋ አይደለም፡፡ የረጅም ዘመናት ህልምህ ይሀዉ ይህንን ደረጃ ደርሷል፡፡

በሌላ በኩል፣ የመጽሀፉን ረቂቅ የስራ ሃላፊነታችሁንና የጊዜ መጣበብን ሳታመካኙ በደስታ ተቀብላችሁ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በማንበብ ጥልቅ አስተያየት የሰጣችሁንን ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን እና አቶ ታደሰ ሲባሞን በእጅጉ እናመሰግናችኋለን፡፡ መረጃ በማሰባሰብ ሂደት ቅንና ትክክለኛ መረጃዎችን በደስታ የሰጣችሁን የእድሜና የህይወት ልምድ ባለጠጋ የሆናችሁትን አባቶች፣ ለተከታይ ትዉልድ የታሪክና የባህል እዉቀታችሁን ለማካፈል በመፍቀዳችሁ አክብሮታችንና ምስጋናችን ትልቅ ነዉ፡፡ በተለይ በሀዲያ ሴራ በተደረገዉ ጥናት መረጃ በማሰባሰብና በማጠናቀር የተሳተፋችሁም እንደዚሁ ትጋታችሁ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

የዚህን መጽሀፍ የሽፋን ዲዛይን ለተጠበበከዉ ቴምድሮስ ብርሃኑ እና ካርታዎችን በመስራት ለተጋሀዉ ተስፋዬ ተሰማ አድናቆታችን እጅግ ነዉ፡፡ በመጨረሻም የመጽሀፉን ረቂቅ ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻ የተየብሽልንን መሰረት ደባልቄን ሳናመሰግንሽ አናልፍም፡፡

# ማውጫ

ገጽ

መግቢያ 1

ክፍል 1፤ የሀዲያ ህዝብ ጠቅላላ ገለጻ 4
1.1. መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ 4
1.2. ቋንቋ 6
ክፍል 2፤ የሀዲያ ህዝብ በተለያዩ ዘመናት 12
2.1. ሀዲያ፣ የቃሉ ትርጓሜ 12
2.2. የሀዲያ ህዝብ መነሻና እንቅስቃሴ እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን 14
2.3. የሀዲያ እስላማዊ መንግስት መገኛ 20
2.4. የሀዲያ እስላማዊ መንግስት ከ13ኛ እስከ 17ኛ ክፍለ ዘመን 22
2.4.1. በሀዲያና በክርስቲያኑ የሰሜን ኢትዮጵያ መንግስት መካከል የነበረዉ በጦርነት ላይ ብቻ የተመሰረተዉ ግንኙነት 23
2.4.2. የጋብቻ ዝምድና በአማራጭ'ት መወሰዱ እና የንግስት እሌኒ ታላቅ ሚና 31
2.4.3. የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት በክርስቲያን ጦርነት ወቅት/1531-1543/ 42
2.4.4. የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ በሀዲያ ህዝብ ላይ ያስከተላቸዉ አዳዲስ ሁኔታዎች 46
2.5. የሀዲያ ህዝብ አጠቃላይ ሁኔታ ከ17ኛ እስከ 19ኛዉ ክፍለ ዘመን 54
2.6. የሀዲያ ህዝብ ታሪክ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻዉ ሩብ እስከ 1974 እ.ም 68
2.6.1. ሀዲያ ከ1894-1935 እ.ም 85
2.6.2.የሀዲያ ህዝብ በጣሊያን ወረራ ዘመን 90
2.6.3. በጣሊያን አስተዳደር ዘመን በሀዲያ የተከሰቱ ጊዜያዊና ዘላቂ ለዉጦች 98
2.7. የሀዲያ ጥንታዊ የፖለቲካዊ ስርአት ግምገማ 114
2.8. የሀዲያ ብሔር የኢኮኖሚ ሁኔታ ዳሰሳ እስከ 1974 እ.ም 121
ክፍል 3፤ የሀዲያ ሴራ (Seera) 137
3.1. የሀዲያ ሴራ ምንነት 137
3.2. በሀዲያ ሴራ (Seera) ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተቋማት 140
3.3. ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትና ሚናቸው 141
3.3. 1. ምኔ /Mine/ ወይም አበሮሳ /Abaroosa/ 141
3.3. 2. ነፈራ /Nafara/ 143
3.3 3. ሞሎ /Moollo/ 146
3.3. 4. ሱሎ /Sullo/ 148
3.3. 5. ጊቾ /Giicho/ 150
3.3. 6. ጊራ /Giira/ 152
3.4. ግጭትና የግጭት አፈታት በሀዲያ ሴራ 154
3.4.1. የግጭት ምንነት፣ ዓይነቶችና ደረጃዎች 154
3.4.2. ሊከሰት የሚችልን ግጭት ጠቋሚዎች 158
3.4.3. ሀድሮ /Hidiro/ 160
3.4.4. ዋነኛዎቹ የግጭት መንስኤዎች 162
3.4.5. የግጭት አፈታት ዘዴዎች 166
3.4.6. ሞትን ያስከተለ ጉዳይ በሴራ መዋቅሮች የሚታይበት መንገድ 172
3.4.7. የጢግ ስነ ስርዓት 180
3.4.8. ሳዕማ /Saa'imma/ ወይም የዝሙት ወንጀል 187
3.4.9. የውሳኔ አፈጻጸም /Enforcement/ ዘዴዎች 192
3.5. ሴቶችና የሀዲያ ሴራ /Seera/ 196

ክፍል 4፣ ሃይማኖት 200
4.1. ፊንዳንና፣ የሀዲያ ጥንታዊ ሃይማኖት 200
4.2. የፊንዳነና እምነት መሰረት 201
4.3. የአምልኮና የመስዋዕት አቀራረብ ስርአት 206
4.4. ጋብቻ በፊንዳነና ሃይማኖት 210
4.5. መንስማ 211
4.6. መሰረታዊ ሃይማኖታዊ ስርዓቶች እና ልምምዶች 214
4.7. ከሞት ወዲያ ህይወት 219

ክፍል 5፣ በሀዲያ ህዝብ ከልደት እስከ ሞት ያሉ ወጎች 229
5.1. የልደት አከባበር ስርአት 229
5.2. የሰዉ ስም አወጣጥ እና አጠራር 234
5.2.1. የልደት ስም 241
5.2.2. ከእንስሳትና ከተፈጥሮ የተወሰዱ ስሞች 244
5.2.3. የማዕረግ ስሞች 245
5.2.4. ሌሎች ስሞች 247
5.2.4.1. ሀይማኖታዊ ስሞች 247
5.2.4.2. የቅጽል እና የስድብ ስሞች 248
5.2.4.3. የጓደኛ መግባቢያ ስሞች፣ ደረጽ-ሱማ (ገበጥ-ሱማ) 249
5.2.4.4. የጋብቻ ስሞች 255
5.3. በሉዊሻ፣ የሴቶች የቋንቋ አጠቃቀም የተለየ ገጽታ 256
5.4. በላቻ /Ballachcha/፣ የግርዛት ስነስርአት አፈጻጸም 267
5.5. በሎቾኦ /Bollochcho'o/፣የጋብቻና የሰርግ ስነስርአት አፈጻጸም 274
5.5.1. ጤአቀንቻ/Xee'aqancha/፣ ትጭጭት 274
5.5.2. የጋብቻ አይነቶች 281
5.5.2.1. ጐሰኖ /Gosano/፣ ጠለፋ 281
5.5.2.2. ሄረንቻ /Heeranchcha/ 282
5.5.2.3. ለጐ /Lago/፣ ውርስ 283
5.5.2.4. እልገና /Ilgana/ 284
5.5.2.5. ለዲሻ /Ladishsha/ 285
5.5.2.5.1. ሆሻሮ /Hoshsharo/ 286
5.5.2.5.2. ለንድሰንቻ/Landisanchcha/ 286
5.5.2.5.3. አንጋቻ /Angachcha/ 287
5.5.2.5.4. እልሞቻ /Ilmocha/ 290
5.5.2.5.5. ኪፋ /Kiiffa/ 290
5.6. ዊዕሎ/Wi'illo/፣ የልቅሶና የሀዘን ስነስርአት 294
5.6.1. በሀዲያ የቀብር ስነስርአት አይነቶችን የሚወስኑ ጉዳዮች 294
5.6.2. የቀብር ስነስርአት 304
5.6.3. ድሀረ ቀብር 309

ክፍል 6፣ ቃላዊ ሀብቶችና ጨዋታዎች 312
6.1. ሸርማ/Sharimma/ 312
6.2. ድራንቻ/Diranchcha/ 318
6.3. ግጦኦ/Gixo'o/ 320
6.4. ያኑዋ /Yannuwwa/፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች 323
6.5. ሄስ ሄሳ ቀሬ /Hees heessa qare/፣ የሀዲይሳ እንቆቅልሽ 335
6.6. ለቦቶ/Labbootto/ 340
ማጠቃለያ 344
ዋቢ መጻህፍት 345

አባሪ 1፣ በኢትዮጵያ ክልሎች የሀዲያ ዞን መገኛ ካርታ 349

አባሪ 2፣ የሀዲያ ዞን ወረዳዎችን የሚያሳይ ካርታ 350

አባሪ 3፣የሀዲያ ካርታ በ15ኛው ክፍለ ዘመን 351

አባሪ 4፣ለፖሊስ ሰራዊት ጠቅላይ መምሪያ የተፃፈ ደብዳቤ 352

አባሪ 5፣ለክቡር የህዝብ ፀጥታ የተሰጠ መልስ 357

አባሪ 6፣ለከምባታ አውራጃ ግዛት ፖሊስ አዛዥ የተፃፈ ደብዳቤ 358




# መግቢያ

የህዝቦች ማንነት በዋናነት የታሪካቸዉና የባህላቸዉ ድምር ዉጤት እንደሆነ ይታመናል። በዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነት በታሪካቸዉና በባህላቸዉ የተገነባ ሆኖ እናገኛለን። ኢትዮጵያም የብሄር ብሄረሰቦቿ እና ህዝቦቿ ድምር ዉጤት የሆነች አገር በመሆኗ፤ ታሪክዋም ሆነ ባህልዋ የብሄር ብሄረሰቦቿ እና ህዝቦቿ ታሪክና ባህል መሆኑ ግልጽ ነዉ። በሌላ አነጋገር፣ የአትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታን መነሻ በማድረግ ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ የሚሆን ኢትዮጵያዊ የሚባል ነጠላ ማንነት (identity) ማግኘትም ሆነ ማሰብ አይቻልም። ይልቁንም ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ማንነት ነፃብራቅ ነዉ ማለት ይቻላል። የማንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ የኋላ ታሪኩና ትስስሩ በጥንቃቄና በታማኝነት ሲታይ ከኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ከአንዱ ወይንም ከብዙ ጋር መያያዙ አይቀሬ ነዉ። ከዚህም በመነሳት ማንኛዉም በኢትዮጵያ የወሰን ክልል የሚኖር ብሄር ብሄረሰብ ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር የተሳሰረ በመሆኑ አባላቱም ኢትዮጵያዊያን ናቸዉ ማለት ይቻላል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ብዙ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የመሰረቷቸዉ አገሮች ታሪካቸዉና ባህላቸዉ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ የእንደነዚህ አገሮች ታሪክና ባህል ሙሉ ሊሆን የሚችለዉ የሁሉም ብሄሮችና ብሄረሰቦች ታሪክና ባህል ተገቢዉን እዉቅና ሲያገኝ ነው። የዚህ አይነቱ አስተሳሰብ እንደ አንዳንድ የታሪክ አጥኝዎች እምነት ተቀባይነት የሌለዉና ብሄራዊ አንድነትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ተደርጎ ይወሰዳል። እንዲያዉም ግራናስቴይን (1998) በአለባቸዉ (2009፡28) እንደተጠቀሰዉ ብሄራዊ ታሪክንና አንድ አይነትና ወጥ ማንነትን ትቶ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ለህብረታሪክና ለህብረ-ባህል እዉቅና መስጠት ታሪክ የሚባለዉን ጉዳይ እንደ መግደል ተደርጎ ይወሰዳል ይላል። በሌላ በኩል ኩክ (2000) በአለባቸዉ (2009፡28) እንደተጠቀሰዉ የአንድ አገር ታሪክና ባህል ለሁሉም ተዋናዮች ተገቢዉን እዉቅናና ትኩረት መስጠት እንዳለበት በመግለፅ፣ ይህ አይነቱ አስተሳሰብ የታሪክና የባህል ግንበታን እንጂ ጥፋትን አያመለክትም በማለት ይገልጻል።

ከላይ የተጠቀሰዉን አስተሳሰብ መነሻ በማድረግ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የተሻለ ብሄራዊ ስሜት ሊያዳብር የሚችለዉ፣ የኢትዮጵያን ህዝቦች ባህልና ታሪክ ጠንቅቆ በመረዳትና ለማንነታቸዉም ተገቢዉን ክብር በመስጠት ነዉ። ከዚህ ዉጭ የሆነ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ጎደሎ የሆነና ምናልባትም ጠባብ የጎሳ ብሄርተኝነትን ብቻ ሊወክል የሚችል ነዉ ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ጠባብ የጎሳ ብሄርተኝነት ለሌሎች ታሪክና ባህል ተገቢዉን እዉቅና በመንፈግ እነርሱ አባል ለሆኑለት ቡድን የበላይነት የሚያቀነቅኑ ብቻ ከመሆን አይዘልምና።

በመሆኑም ይህ የሀዲያ ህዝብ ታሪክና ባህል በሚል ርዕስ የተጻፈዉ መጽሀፍ መሰረታዊ አስተዋተጽኦ የሚሆነዉ የኢትዮጵያዊያንን የብሄራዊ ማንነት እዉቀትና ስሜት በተሻለ ደረጃ ከፍ በማድረግ ስለ ኢትዮጵያና ህዝቦቿ ያለንን እዉቀት ምልኣት ያለዉ እንዲሆን ማገዝ ነዉ።

ይህ መጽሀፍ ታሪኩንና ባህሉን ቀንጭቦ የሚያወሳለት የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ጋር ያለዉን አንድነቱንና ልዩነቱን የመጽሀፉ አንባቢ ይረዳል የሚል እምነት ጸሀፊዎቹ አላቸዉ። ስለዚህ መጽሀፉ ሀዲያነትን ማለትም የሀዲያ ህዝብ የራሱ ማንነት መገለጫ የሆኑ የታሪክና የባህል ገጽታዎችን በማንሳት የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚለይባቸዉን የማንነቱን ገጽታዎች ያስቃኛል። በዚህ ሂደት የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ጋር ያደረጋቸዉን ትግሎች፣ ድሎችና ሽንፈቶች በማዉሳትም የሀዲያ ህዝብ ከሌሎች ህዝቦች ጋር ያለዉን ጥብቅ ታሪካዊ ትስስርና ቁርኝት ያመለክታል።

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ፣ ይህ መጽሀፍ ምንም እንኳን የሀዲያ ህዝብ ታሪክና ባህል በሚል ርዕስ ቢጻፍም፤ የኢትዮጵያዊነት አንዱ አካል የሆነዉን ህዝብ ታሪክና ባህል የተለያዩ ገጽታዎችን ማስገንዘቡ፣ ለማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ኢትዮጵያዊነትን ከማጣጣም (ከማድነቅ) አንጻር ጠቀሜታዉ የጎላ ይሆናል የሚል እምነት የመጽሀፉ ደራሲዎች አላቸዉ።





መጽሀፉ በዉስጣዊ ይዘቱ የህዝቡን መልክአምድራዊ አቀማመጥና ቋንቋዉን በመጀመሪያ ክፍል ጠቁሞ፣ በክፍል ሁለት የሀዲያ ህዝብ ከጥንት እስከ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ያለፈበትን ታሪካዊ ጉዞ ያስቃኛል። ቀጥሎም የሀዲያ ሴራ ከነመዋቅሮቹና ከሚናቸዉ ጋር በክፍል ሶስት የቀረበ ሲሆን፣ በክፍል አራት ደግሞ የሀዲያ ህዝብ ጥንታዊ ሃይማኖት (ፊንዳነና) ቀርቧል። በክፍል አምስት በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ከልደት እስከ ሞት ያሉ ወጎች (ልደት፣ የስም አወጣጥ፣ ግርዘት፣ ጋብቻና ሞት) በተለያዩ ምሳሌዎች ተስፋፍተዉ የቀረቡ ሲሆን፣ በክፍል ስድስት ስር በባህሉ ዉስጥ ያሉ ስነጽሁፋዊ ቃና ያላቸዉ ቃላዊ ሀብቶችና ጫዋታዎች ቀርበዋል።

በአጠቃላይ፣ በዚህ መጽሀፍ ከህዝቡ ታሪክና ባህል አንጻር ህዝቡን ሊገልጹ የሚችሉ ዋና ዋና ገጽታዎችን በማንሳት ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል። ከዚህ መጽሀፍ በዋናነት፤ የታሪክ፣ የባህል፣ የስነልሳን፣ የስርአተጾታ፣ የቲአትር ጥበባት፣ የስነጽሁፍና የፎክሎር ተመራማሪዎች የመረጃ ምንጭነትን ትሩፋት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ የመጽሀፉ አዘጋጆች ያምናሉ። በመጽሀፉ ዉስጥ የተ ጠቀሱ የታሪክና የባህሉ ቁልፍ ቃላት፣ ስነልሳናዊና ስነጽሁፋዊ ምሳሌዎችም እንዲሁ በላቲን ፊደላት የአነባበብ ስርአታቸዉን በሚያሳይ መልኩ ቀርበዋል። ጸሀፊዎቹ ይህን ያደረጉበት ምክንያት፣ አንባቢ እነዚያን ቃላት የቋንቋዉ ተናጋሪ እንደሚጠራቸዉ አድርጎ እንዲያነብ ያስችለዋል ብለዉ ስላሰቡ ነዉ። በዚህ መጽሀፍ ዉስጥ የተጠቀሱት ዘመናት ተለይቶ (እ.ኢ.አ ተብሎ) ከተጠቀሰዉ ዉጭ ሁሉም በአዉሮፓዉያን አቆጣጠር የተጠቀሱ ናቸዉ።

መልካም ንባብ

አለባቸዉ ኬዕሚሶ
እና
ሳሙኤል ሀንዳሞ
ሀምሌ 2002 አ.ም
አዲስ አበባ

# ክፍል 1፤ የሀዲያ ህዝብ ጠቅላላ ገለጻ

## 1.1. መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ

በአሁኑ ጊዜ የሀዲይሳ ተናጋሪ ህዝቦች በዋናነት በደቡብ ህዝቦች እና ብሄር ብሄረሰቦች ክልላዊ መንግሥት በሀዲያ ዞን ይኖራሉ፡፡ የሀዲያ ዞን የማእከላዊ ኢትዮጵያን የደጋ ክልሎች ለሁለት ከሚከፍለው ስምጥ ሸለቆ በስተ ምዕራብ 7$^0$ እና 45' ሰሜን 38$^0$ እና 28' ምስራቅ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ዞኑ በአስር ወረዳዎች እና በአንድ የከተማ አስተዳደር (ሆሳዕና ከተማ) ተከፍሏል[1]፡፡ የሀዲያ ዞን ዋና ከተማ የሆነችው ሆሳዕና ከተማ ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ ምእራም 230 ኪ..ሜ. ላይ ትገኛለች፡፡

የ1997 እ.ኢ.አ. የህዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መረጃ እንደሚያመለክተው ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ብቻ የሚኖሩ ሀዲይሳን እንደ አፍ መፍቻቸው የሚናገሩ ህዝቦች ቁጥር 1,284,366 ያህል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ፣ በዚሁ መረጃ ሀዲይሳ በኢትዮጵያ ከሚነገሩ ቋንቋዎች በተናጋሪ ብዛት 8ኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቋንቋ ነው፡፡

የሀዲያ ዞን በመልክአ ምድራዊ አቀማመጡ፤ በሰሜን ከጉራጌ፣ በሰሜን ምስራቅ ከስልጤ፣ በደቡብ ከወላይታ፣ በምስራቅ ከከምባታ፣በደቡብ ምእራብ ከጠምባሮ እና በምእራብ

[1] በአባሪ ላይ ካርታ ሁለትን ይመለከቷል፡፡





ከግቤ ወንዝ እና ከየም ልዩ ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡ ከእነዚህ አጐራባች ህዝቦች ጋር ባላቸዉ ሰፊ ግንኙነት ምክንያት በድንበር አካባቢ የሚኖሩ አብዛኛዎቹ የሀዲያ ህዝቦች ልሳነ. ክልኤ[2] ወይም ልሳነ ብዙ (bi/multilinguals) ናቸው፡፡

ዞኑ በሶስት ዋና ዋና የአየር ጠባይ(climate) እና የከፍታ (altitude) ዞኖች የተከፈለ ነው፤እነሱም *ሀንሰዋ* (ደጋ)፣ *ሀንሰው ቃለዓ* (ወይና ደጋ) እና *ቃላዓ* (ቆላ) የሚባሉ ናቸዉ፡፡ በእነዚህ የአየር ጸባዮች የሚመረቱት የሰብል አይነቶች እንደየአካባቢው የተለያዩ ናቸው[3]፡፡ በዞኑ በዋናነት ከሚጠቀሱ የሰብል አይነቶች ስንዴ (በተለይ በወይና ደጋ)፣ ጤፍ (በቆላ) እና ገብስ እና አተር (በደጋ) የአየር ጸባይ የሚመረቱ ናቸው፡፡ ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የአየር ጸባይ በሌላ መልኩ የሀዲያ ህዝብ በተለምዶ የአየር ጸባይ ክልል የሚያሳዩ ዞኖችን በሁለት ሰፊ ክፍሎች ይከፋፍላል፤ *ሀንሰዋ* (የወይና ደጋ እና የደጋ አካባቢን ያጠቃልላል) እና *ቃለዓ* (ቆላ) በማለት፡፡ በአጠቃላይ የሀዲያ ዞን መልክአ ምድራዊ አቀማመጡን በጣም ዝቅተኛ ስፍራ 800 ሜ ያለው የጊቤ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ ሲሆን፣ ከፍተኛ ስፍራ ሴንግዬ (2972 ሜ) በዱና ወረዳ የሚገኘው ነው[4]፡፡

[2] ልሳነ-ክልኤ (bilingual)፣ አንድ ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ሁለት ቋንቋ ዎችን መቻልን የሚያመለክት ቃል ሲሆን፤ ልሳነ-ብዙ (multilingual) የሚለዉ በተለምዶ ከሁለት በላይ ቋንቋዎችን መቻልን አመልካች ቃል ነዉ፡፡

[3] በየነ ዶእልቾ በጌዲዮን (2008፡2) እንደተጠቀሰዉ፡፡

[4] Hadiyya Zone Finance and Economic Development Coordination main Department,1998 E.C, p7. Hossana ፣ ኤርሲዶ ኤርሲዶ (2006) በጌዲዎን እንደተጠቀሰዉ

አመቱን ሙሉ ከሚፈሱ ወንዞች ጉምቦራ፣ ዋራ፣ ዳጉባ፣ ጊቤ፣ ገሙና፣ አጃቾ፣ ግንግታ እና ልንታላ የሚጠቀሱ ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪ ሌሎች አጭር ወቅታዊ ወንዞች በብዛት ይገኛሉ። ከወንዞቹ ሁሉ በርዝመት ትልቁ የዋራ ወንዝ ሲሆን፣ ርዝመቱም 116 ኪ.ሜ. ይሸፍናል። በጥቅሉ በአሁኑ ጊዜ እየተደረገ ካለዉ ዉስን ጥረት በስተቀር ሁሉም ወንዞች ለመስኖ እና ለትራንስፖርት በጉልህ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋሉ አይደሉም[5]። በሌላ በኩል በዞኑ ዉስጥ ያሉትን ሀይቆች በሚመለከት፤ በሻሾጉ ከምትገኘው ከትንሿ የቦዩ ሀይቅ በተጨማሪ በምስራቅ ባደዋቾ ወረዳ ቡደመዳ፣ ጥዕሎ፣ እና መጨፈራ የሚባሉ ሀይቆች አሉ።

## 1.2. ቋንቋ

ሀዲይሳ፣ የሀዲያ ህዝብ የሚጠቀምበት ቋንቋ ሲሆን ስነልሳናዊ አከፋፈሉም የደጋ ምስራቅ ኩሻዊ ቋንቋዎች ቤተሰብ አካል ነው። በሌላ አነጋገር፣ ቋንቋው በአፍሮ እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ ከሚካተቱት የደጋ ምስራቅ ኩሻዊ ቋንቋዎች ከሆኑት ከሲዳምኛ/ሲዳሙ-አፎ /Sidaamuafo/፣ ከከምባትኛ /ከምባትሰታ/kambaatissata/፣ ከጌድኦኛ/ጌዶፋ/ Gedeoffa/፣ከቡርጂ እና አላብኛ /አላብሳ/Alaabisa/ ጋር በቅርብ ቤተሰብነት የሚመደብ ነው። የውጭ አገር ጸሀፊዎች (እነርሱን ተከትለው የአገር ውስጥ ጸሀፊዎች) ቡተሰምዶ የሀዲያ ህዝብና ቋንቋውን *ሀዲያ* በማለት ሲጽፉ ይስተዋላል። ይህ ስያሜ፣ የቋንቋውን ተናጋሪ ማህበረሰብንና ማህበረሰቡ የሚናገረውን ቋንቋ ለይቶ የማይገልጽ በመሆኑ አሻሚነት የሚታይበት ነው። በአንጻሩ አንድ ሀዲያ የሆነ ግለሰብ፣ የራሱን ብሄረሰብ *ሀዲያ* ብሎ ሲጠራ

[5] Hadiyya Zone Finance and Economic Development Coordination main Department, 1998 E.C, p9. Hossana.





ቋንቋውን *ሀዲይሳ* (Hadiyyisa) ወይም *ሀዲይ-ሱሜ* (Hadiyy suume) በማለት ይጠራል። Hadiyyisa በሚለው ቃል ውስጥ /-isa/ የሚለው ቅጥያ ተግባሩ የሀዲያን ህዝብ ቋንቋን መግለጽ ሲሆን በአማርኛ ቅርጽ ፍቺው /-ኛ/ እንደ ማለት ነው። ለዚህም ነው ሀዲይሳ በአማርኛ ቅርጽ ሲነገር ሀዲይኛ በመባል ሲጠራ የሚሰማው። በሌላ በኩል፣ *ሀዲይ ሱሜ* የሚለው ቋንቋዉ የሚጠራበት ሌላው ስያሜው ሲሆን ይህም "የሀዲያ አፍ" የሚል ቀጥተኛ ፍች አለው። ከእነዚህ ከሁለቱ ስያሜዎች በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ እጅጉን ተዘውታሪ ሆኖ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው *ሀዲይሳ* የሚለው ነው። ለዚህ ምክንያቱ ቃሉ ወይም ሀዲይሳ ከአጭርነቱ የተነሳ ለአጠራር አመቺ መሆኑ ነው።

ሀዲያ እንደአብዛኛዉ ህዝብ በስርአት የተደራጀ ማህበረ-ባህላዊ አወቃቀር ያለው ህዝብ በመሆኑ ቋንቋው በስነቃሎች የበለጸገ ነው፤ ምክንያቱም እነዚያን ማህበረ-ባህላዊ መዋቅሮችን የሚያሳዩ እሳቤዎች (concepts) እና ክዋኔዎች በቋንቋ አማካይነት መገለጽ አለባቸውና። ይህ ሲሆን ነው ባህሉ (አጠቃላይ የአኗኗር ስርአቱ) ዘመን ዘለል ሆኖ በቋንቋ አማካይነት ከትውልድ ትውልድ ተሸጋጋሪነቱን የሚያጠናክረው። ሀዲይሳ፣ በቋንቋ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆን በጉረቤት ባሉት ብሄረሰቦች ዘንድም እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ይነገራል። ይህ ጉልቶ የሚታየው ለሀዲያሳ ቋንቋ ድንበር አካባቢ ባሉት የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ ነው። ይህንን አስመልክቶ ሃይሌ (1972፡ 161) እንዲህ በማለት ጽፏል።

*ሀዲይሳ፣ በአብዛኛው አጐራባች ህዝቦች ማለትም፤በከምባታ፣ በሀላባ፣ በጉራጌና በወላይታ ህዝቦች ዘንድ በሁለተኛ ቋንቋነት በሰፊው ይነገራል። እነዚህ ህዝቦች ቋንቋውን ከመናገር አልፈው ለልጆቻቸው ስም ለመስጠት፣ ለፎክሎርና ለዘፈኖች እንዲሁም ለጦር ሽለላዎችና ለሙሾ ስርአቶች ሲገለገሉ ይታያሉ።*

ምንም እንኳን የሀዲይሳን ዘዬ በሚመለከት የዳበረ ስነልሳናዊ ጥናት ባይደረግበትም አንዳንድ አጥኚዎች ወይም ጸሀፊዎች ወደ አምስት የሚደርሱ ዘዬዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ። እነዚህም፤ የሶሮ፣ የሌሞ፣ የሻሾጐ፣ የባዳዋቾ እና የሊብዶ[6] ወይም የማረቆ በመባል የተከፈሉ ናቸው (ተስፋዬ 2009:455) ። ከእነዚህ ዘዬዎች በሰፊ ስርጭታቸዉ የሚታወቁት የሌሞና የሶሮ ሲሆኑ፤ የሶሮ ሀዲይሳ ከሌሎቹ ዘዬዎች ይልቅ ወጥነት (uniformity) እንዳለዉ ይነገራል (ጌታሁን 1993:12)።

የባደዋቾ ዘዬ በመልከአ ምድራዊ አቀማመጡ ከሀዲይሳ ቋንቋ ተናጋሪዎች ድንበራዊ ንክኪ የሌለው ሆኖ በሌሎች ቋንቋዎች ወይም የቋንቋ ተናጋሪዎች የተከበበ ነው። በባደዋቾ የሚነገረው የሀዲይሳ ዘዬ በደቡብ ከወላይታ፣ በምእራብና በሰሜን ከከምባታ፣ በምስራቅ ከአላባና ከአሩሲ ጋር ይዋሰናል። በዚህ ሁኔታ ሰፍረው ያሉ የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች በተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ዘወትር የሚገናኙ ናቸው። እንደማህበራዊ ስነልሳን (Sociolinguistics) አስተሳሰብ የዚህ አይነቱ የህዝቦች ንክኪ የቋንቋዎችን ንክኪ እንደሚፈጥር ይታመናል።

[6]በአሁን ጊዜ የልብዶ ዘዬ ራሱን የቻለ ቋንቋ እንደሆነ የሚናገሩ ወገኖች ያሉ ሲሆን ይህንን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስነልሳናዊ መረጃዎችን ወስዶ ሰፊ ጥናት ማድረግን ይጠይቃል።






ሾኔ[7] ከተማ ላይ የተደረው ጥናት እንደሚያሳየው፣ በአካባቢው(ሾኔ) የሚነገረው የሀዲይሳ ዘዬ ከአካባቢ ዉጭ ባሉት የሀዲያ ዞን አካባቢዎች ከሚነገረዉ ተለይቶ እስከሚታወቅ ድረስ የቋንቋ ዉሰትና መዛነቅ[8] (borrowing and code-switching) የሚታይበት ነው (ሳሙኤል፣ 2009)። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በዚያ ከተማና አካባቢው የሚገኙ የሀዲይሳ ተናጋሪዎች ከአማርኛ ቀጥሎ ወላይትኛ/ወላይታቶ/ን፣ ከምባትኛ/ከምባትሰታ/ን እና ኦሮምኛ/ አፋን ኦሮሞ/ን በቅደም ተከተላቸው እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚናገሯቸው በመሆኑ ነው። እንደዚህ አይነቱ የሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋ መቻል ለቋንቋ ዉሰትና መዛነቅ መሰረት እንደጣለ መገንዘብ ተችሏል (ዝኒ ከመሁ)።

ቀደም ሲል የሀዲይሳ ዘዬዎች እንደሆኑ ከተጠቀሱት ሶሮ፣ ሌሞ እና ሻሾጐ በወሰን መስመሮች ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖራቸው ልብዶና ባደዋቾ ቀጥተኛ የድንበር ግንኙነት የላቸውም። በዚህም ሳቢያ ነው ዘዬዎቹ የቃላትና የድምጾች ልዩነት ከሌሎች ዘዬዎች ይልቅ እንዲሰፋ ምክንያት የሆነዉ።

[7] ሾኔ፣ የምስራቅ ባደዋቾ ወረዳ ዋና ከተማ ሲሆን ከሻሼ-መኔ ወደ አርባምንጭ በሚወስደዉ መንገድ ከአዲስ አበባ 345 ኪ.ሜ ሪቀ በሀዲያ ዞን ይገኛል።

[8] የቋንቋ ዉሰት/borrowing/ የሚባለዉ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ከሌላ ቋንቋ በተለይም ቃላትን ወስዶ በሚናገረዉ ቋንቋ (አብዛኛዉን ጊዜ በመጀመሪያ ቋንቋዉ) አስገብቶ መጠቀም ነዉ። ዉሰት ብዙ ጊዜ የቃላት እጥረትን ምክንያት የሚያደርግ ሲሆን፤ የቋንቋ መዛነቅ የሚባለዉ ግን፣ ባንድ ቋንቋ ሀሳብ መግለጽ እየተቻለ የሌላን ቋንቋ ቃላትን፣ ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን ወደ አንድ ቋንቋ አስገብቶ መጠቀምን አመልካች ቃል ነዉ። የዉሰት መነሻዉ የቃላት እጥረት' ሲሆን የመዛነቅ /code-switching/ ግን ቅንጦት ወይም ቃላትን አስቦ /መርጦ/ ለመናገር መታከት ወይም ሁለተኛ ቋንቋን እየቀላቀሉ ማዉራትን እንደ ኩራት መቁጠር ሲሆን ይችላል።

እነዚህ እንደ ዘዬ የሚቆጠሩት የሀዲይሳ ቅርጾች የተወሰነ የአነጋገር ልዩነት ቢኖራቸውም ባንድ ቋንቋ ማለትም በሀዲይሳ ስር ተጠቃለው የሚጠሩ ናቸው:: የሀዲይሳን የዘር ግንዱን በሚመለከት በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ ማሳየት ይቻላል::




(ከ'Bender፣ 1976፡ 232' ተሻሽሎ የተወሰደ)

በአሁኑ ጊዜ የሀዲይሳ ቋንቋ በዞኑ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል እንደ ማስተማሪያ ቋንቋ፣ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ደግሞ እንደ አንድ የትምህርት አይነት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ሀዲይሳ ለአጻጻፍ ስርአቱ እየተጠቀመ ያለው የላቲን ፊደላትን ሲሆን፣ ቋንቋውን በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃም እንደ አንድ የትምህርት አይነት ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል::





ከዚህ በመቀጠል በሀዲይሳ ዉስጥ ያሉ 22 ተናባቢና[9] 5 አናባቢ ድምጾች ከሳባ ፊደላት አንጻር ቀርበዋል::

## *የሀዲይሳ ተናባቢና አናባቢ ድምጾች የተወከሉባቸዉ ድምጸልሳናት[10]*

| በላቲን | በሳባ | በላቲን | በሳባ |
|---|---|---|---|
| a | አ | o | ኦ |
| b | በ | q | ቀ |
| c | ጨ | r | ረ |
| d | ደ | s | ሰ |
| e | ኤ | t | ተ |
| f | ፈ | u | ኡ |
| g | ገ | w | ወ |
| h | ሀ | x | ጠ |
| i | ኢ | y | የ |
| j | ጀ | z | ዘ |
| k | ከ | ch | ቸ |
| l | ለ | sh | ሸ |
| m | መ | ph | ጰ |
| n | ነ | | |

[9] በስነልሳን የጎሮሮ እግድ ድምጽን ለማሳየት የራሱ ወካይ ድምጽ ያለዉ ሲሆን በሀዲይሳ (በላቲን አጻጻፍ) ፊደል አልተቀረጸለትም፤ሆኖም ይህንን ድምጽ ለመወከል ይህ (') ምልክት ይደረጋል:: ለምሳሌ፣ Waa'a 'አምላክ'፣ Aa'e 'ተቀበል'፣ Wo'lla 'ጥጃ' በሚሉ ቃላት (') ምልክት ባረፈበት ቃሉ ጎሮሮ ዉስጥ ረገጥ ተደርጎ ይነበባል::

[10] በሀዲይሳ አምስት አጭርና አምስት ረጅም አናባቢዎች ያሉት ሲሆን፣ የአነባበብ ርዝመቱን ለማመልከት አናባቢዉ ተደግሞ ይጻፋል:: አጭር የተባሉ አናባቢዎች፤ a፣ e፣ i፣ o እና u ሲሆኑ፣ ረጅም የሚባሉት ደግሞ፤ aa፣ ee፣ ii፣ oo ና uu ናቸዉ:: የአናባቢዎች ማጠርና መርዘም በሀዲይሳ የትርጉም ለዉጥ ያመጣል:: ለምሳሌ፣ ite 'ብላ' የሚለዉ ሲረዝም iite 'ዉደድ' ሲሆን፣ age 'ጠጣ' የሚለዉም በተመሳሳይ ሁኔታ aage 'ግባ' ይሆናል::

# ክፍል 2፤ የሀዲያ ህዝብ በተለያዩ ዘመናት

## 2.1. ሀዲያ[11]፣ የቃሉ ትርጓሜ

ተጽፈው በተቀመጡ የታሪክ ሰነዶችና በሀዲያ ህዝብ አፈ ታሪክ ሀዲያ የሚለው ቃል በርከት ያሉ ትርጓሜዎች ያሉት ቃል ነው፡፡ ከራሱ ከሀዲያ ህዝብ በተጨማሪ የተለያዩ ወገኖች ሀዲያ ለሚለው ቃል የየራሳቸውን ትርጓሜዎች ሰጥተዋል፡፡ሀዲያ ለሚለዉ ቃል የተለያዩ ወገኖች የሰጡትን ትሩጓሜዎችን በብራዉከምፔር (2004፡ 56) ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዱ አሩሲዎች የሰጡት ትርጓሜ ነዉ፡፡ አሩሲዎች ሀዲያ የሚለውን ቃል ሲተረጉሙ ከነብዩ መሐመድ ቅዱስ ቃሉን የተቀበሉ ወይንም የመሬቱ ባለቤቶች ለማለት እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡ በጨርጨር አካባቢ ደግሞ ሀዲያ የሚለው ቃል እዚያው የቀሩ ለሚለው ሀሳብ ተመጣጣኝ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ ተመጣጣኝ ተደርጐ የሚወሰድበትንም ምክንያት ሲገልጹ የራሳቸዉ ወገን የሆነው ህዝብ ከአካባቢው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሲሰደድ ያልተቀላቀሉ መሆናቸውን ለመግለፅ እንደሆነ ይነገራል፡፡ የጂሃድ ሠራዊት ሀዲያ የሚለውን ቃል የአምላክ ስጦታ ለማለት እንደተጠቀመው ሲገለጽ በሀዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ካገኙ ትርጓሜዎች ይህ ዋነኛው ነው፡፡ ነገር ግን ግራኝ አህመድ ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር የተዋጋበት

[11]ሀዲያ /Hadiyya/ የሚላዉ ቃል (ብራዉካምፔር 2004 ፡ 55) አንዳንድ ጊዜ Hadya, Hadea, Hadija, Hadiyo, Hadyeh, Adia, Adea በሚሉ ቃላት ተፅፎ ቢገኝም (ብራዉካምፔር 1973 ፡ 55) ሁሉም የዛሬዉን የሀዲያ ህዝብ እንደሚያመልክቱ ገልጿዋል፡፡





16ኛው ክፍለ ዘመን ሀዲያ የሚለው ቃል በጽሁፍ እንኳን ለፍሮ ከተገኘበት የ13ኛው ክፍለ ዘመን ረጅም ዓመታት በኋላ የተሰጠ ትርጉም መሆኑ የቃሉን ዕድሜ አመላካች አለመሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የሀዲያ ህዝብ ሀዲያ የሚለውን ቃል ሲተረጉም የአረብን ባህረ ሰላጤ ለቆ፣ አዲስ መሬት ፍለጋ ቀይ ባህርን አቋርጦ ወደ አበሻ ምድር የገባው የመጀመሪያ ሰው ስም ነው ብለው ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ሀዲያ የሚለው ቃል ትርጉሙ ከሁለት የሀዲይሳ /Hadiyyisa/ ቃላት ጥምረት የተፈጠረ ቃል እንደሆነ ይገልፃል፡፡ እነርሱም ሀድ /Had/ እና እያ /iyya/ የሚሉ ናቸው፡፡ ሀድ /Hade/ ማለት ሁሉ ወይንም ህዝብ ሲሆን እያ /-iyya/ ማለት ደግሞ ተሸካሚ፣ ትእግስተኛ፣ታጋሽ የሚለውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ስለዚህ ሀድእያ /Hadiyya/ /ሀዲያ/ /Hadiyya/ ማለት ሁሉን ወይም ህዝብን የሚሸከም ማለት እንደሆነ ይነገራል፡፡ እላይ ከተጠቀሱት የተለያዩ ትርጓሜዎች በመነሳት ሀዲያ የሚለው ቃል ከተለያዩ መነሻዎች የተለያየ ትርጓሜ ቢሰጠውም እያንዳንዱ ትርጉም ስለ ሀዲያ ህዝብ የራሱ የሆነ መልዕክት ያዘለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሀዲያ የሚለው ቃል በሀዲያ ህዝብ አጠቃላይ የታሪክ ዘመናት የህዝብ የወል መጠሪያ ሆኖ መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2. የሀዲያ ህዝብ መነሻና እንቅስቃሴ እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን

በጽሁፍ የሰፈሩ መረጃዎችና የህዝቡ አፈታሪክ የሀዲያን ህዝብ መነሻ ከእሲያ የባህር ዳርቻ እስከ ሰሜናዊው የዛሬው የኢትዮጵያ ክፍል ባለው ሰፊ ቦታ ላይ ይጠቁማሉ። በመሆኑም ስለሀዲያ ህዝብ መነሻ ሁሉንም ወገኖች የሚያስማማ አንድ ቦታ መጠቆም አስቸጋሪ ይሆናል።

ለምሳሌ፣ በሀዲያ ህዝብ አፈ ታሪክ መሠረት የሀዲያ ህዝብ የመጀመሪያ መነሻ በእስያ የባህር ዳርቻ ከሚገኘው የአረቢያ ባህረ ገብ መሬት ሲሆን የሀዲያ ህዝብም በቀይ ባህር በማቋረጥ በሰሜን ኢትዮጵያ የሰፈረ የመጀመሪያ ህዝብ ነው ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም የሀዲያ አፈታሪክ ሀዲያ ከአረብ ባህረ ሰላጤ የተንቀሳቀሰበትን አቅጣጫ በመጠቆምና በጉዞውም መጨረሻ የሰፈረበትን ቦታ በማሳየት የሀዲያ ህዝብ የኢትዮጵያ ቀደምት ነዋሪዎች መሆናቸውን ይጠቁማል።

በምሥራቅ አፍሪካ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በተለይም መነሻቸውን በአረቡ ባህረ ገብ መሬቶች መጠቆማቸው የተለመደ የአፈ ታሪካቸው አካል ነው። ከዚህ በመነሳት የሀዲያም ህዝብ ተመሳሳይ የሆነ የአፈ ታሪክ መረጃ መጠቀሙ ብዙም የሚገርም አይደለም። የዚህ ዓይነቱን የአፍሪካ ታሪክ አስተሳሰብና አፃፃፍን ፍልፕሰን (1998፡58) ሲያብራራ

> *በቀደሙት የአፍሪካ የታሪክ ጥናቶች በአፍሪካ ውስጥ የነበሩትን ጥንታዊ ማህረሰቦችና ውስብሰብ ስልጣኔዎችን ለመተንተን የውጭ ተፅዕኖን እንደ ምክንያት መጠቀም የተለመደ ነበረ። በዚህ ተመሳሳይ የታሪክ አስተሳሰብና ትንተና መሠረት ዋና ዋናዎቹ*





> *አፍሪካዊ ስልጣኔዎች ለምሳሌ የግብፅ የቤኒን፣ የዝምባቡዌ፣ እና የኢትዮጵያን ጥንታዊ ስልጣኔዎች የካውካሰስ ህዝቦች ተፅዕኖ ውጤቶች መሆናቸውን ለማሳየት ከፍተኛ ጥረቶች ተደርገዋል።*

ይህ አስተሳሰብ የበላይነትና ከፍተኛ ተቀባይነት የነበረው የሰው ዘር መገኛ አፍሪካ በአጠቃለይና ኢትዮጵያ በተለይ መሆኑ ከመረጋገጡ በፊት በነበሩት ዘመናት ነበረ። በአሁኑ ወቅት የተገኙት የአርኪዮሎጂ ጥናት ውጤቶች እንዳረጋገጡት ረጅሙን ዕድሜ ያስቆጠረው የሰው ዘር አፅም የተገኘው በኢትዮጵያ በአዋሽ ዝቅተኛ ቦታዎች ነው[12]።

ስለዚህ በሀዲያ አፈ ታሪክ እንደሚነገረው በሰሜን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈረው ሰውና ህዝብ (ሀዲያ) የመጣው ከአረብ ባህረ ገብ መሬት ቀይ ባህርን በማቋረጥ ነው የሚለው ትንተና ብዙም ታሪካዊ ፋይዳ ያለው ሆኖ አናገኘውም። በተለይም የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ "የመጣን" አስተሳሰብ መረጃ የማይገኝለትና እውነትነቱ እጅግ አጠራጣሪ ነው።

ምንም እንኳን ከአረብ ባህረ ገብ መሬት ቀይ ባህርን አቋርጠን ወደ ሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል መጠን የሚለው አስተሳሰብ በማስረጃ ለማስደገፍና ለመቀበል አዳጋች ቢሆንም የሀዲያ ህዝብ የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል ለመጀመሪያ ጊዜ ተቆጣጥረውት የነበሩ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች እንደነበሩ የታሪክ አጥኚዎችና ፀሐፊዎች ይስማማሉ (ሰረገው 1964፣ ሀይሌ ቡባሞ 1973፣ ፊልፕሰን ፣ 1998) ።

[12] 4.4 ሚሊየን ኣመት እድሜ ያስቆጠረዉን የአርዲን /Ardipithicus ramidus/ አፅም መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህ የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪና የመጀመሪያዎቹ የሰሜኑ የኢትዮጵያን ክፍል ተቆጣጥረውት የነበሩት ህዝቦች እነማን ናቸው ለሚለዉ ጥያቄ ሀይሌ ቡባሞ (1972) ዲልማን (1948)'ን በመጥቀስ እንደገለፀው የአንጌቦ መንግሥት በአክሱም ለሁለት መቶ አመታት ያህል መንገሱን ይናገራል፡፡ ሀይሌ ቡባሞ የተለያዩ ምንጮችን[13] በመጠቀም የአንጌቦ መንግሥት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የመጀመሪያው ጥንታዊ መንግሥት እንደነበር ይጠቁማል፡፡

አንጌቦ የሚለው ስም የሀዲይሳ መነሻ ያለውና ዛሬም በሀዲያ ህዝብ ዘንድ የግለሰብ ሥም ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ ትርጓሜውም በሀዲይሳ /Hadiyyisa/ ምርኮ ማምጣት ሊባል ይችላል፡፡

ከዚሁ የሀይሌ አስተሳሰብ ጋር በተወሰነ ደረጃ ሊመሳሰል የሚችል ሌቪን (1993፣16) የጠቀሰው ሐሳብ ሲሆን በዚህ ፀሃፊ ገለፃ የመጀመሪያው የሀዲያ ንጉስ አንጎ /Ango/ ሲሆን ልጅም አዳ /Ada/ ይበል ነበረ፡፡ በመሆኑም "አንጌቦ" የሚለው የሀዲይሳ /Hadiyyisa/ ስም ስናሳጥረዉ "አንጎ" /Ango/ የመባሉ ሆኔታ የተለመደ መሆኑ የአንጌቦ መንግሥትን በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ አስተሳሰብ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆኑ ከሚችሉት ተመሣሣይ የሀዲይሳ ስያሜዎችና ሲያጥሩ ከሚፈጥሩት ስያሜዎች መካከል የሚከተሉትን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡

[13] ድልማን (1848፡ 26) እና በጅ( 1922፡ 35), (1966፡ 192-193)





| ሙሉ ስም | | የቁልምጫ ስም /ያጠረ ስም/ |
|---|---|---|
| Uulloro | > | Uullo |
| Sulluro | > | Sullo |
| Angeebo | > | Ango |
| Xilahune | > | Xilo |
| Latiso | > | Lato |
| Hanqore | > | Hanqo |

የሀዲያ ህዝብ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ጥንታዊ ነዋሪ ህዝብ መሆኑን የሚደግፈውና ተጨማሪ መነሻ ሊሆነን የሚችለዉ የሀበርላንድ (1972፡ 5) ሀሳብ ነው፡፡ ሀበርላንድ እንደገለፀው ከደቡብ አረቢያ ወደ ሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በአሰብ በኩል የገቡት የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ወደ አማራ ሳይንትና አንጎት ሲደርሱ እዚያ አካባቢ ነዋሪ በሆኑት የአገውና የሀዲያ ህዝብ ተውጠው ቀርተዋል፡፡ ይህ የሀበርላንድ አስተሳሰብ የሀዲያ ህዝብ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከመጀመሪያው የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ከደቡብ አረቢያ ወደ አካባቢው መግባት ጀምሮ (ከ1ኛ እልፍ ዓመት የክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ) እንደነበሩ ማረጋገጫ ነው፡፡

እላይ ከተገለጹት ታሪካዊ መስረጃዎች በተጨማሪ ሀይሌ (1972) ሀዲይሳ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ባሉት ቋንቋዎች ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በመተንተን የሀዲያ ህዝብ ዛሬ ወደሰፈረበት አካባቢ የተንቀሳቀሰው ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እንደነበረ ይከራከራል፡፡

በሀዲያ ህዝብ አፈ-ታሪክም መሠረት የሀዲያ ህዝብ ወደ ዛሬው የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል ከመንቀሳቀሱ በፊት መኖሪያው በተወሰኑ የትግራይ ክፍሎችና በወሎ አካባቢ እንደነበረ ይገለፃል። የሀዲያ ህዝብ ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ቀስ በቀስ ወደ ደቡብ ላደረገው እንቅስቃሴ የተለያዩ ጉዳዮች እንደምክንያት ይገለፃሉ። ለምሳሌ የክርስቲያኑ የሰሜን ኢትዮጵያ መንግሥት ጥንካሬና መስፋፋት፣ የህዝቡ ኢኮኖሚ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን በአብዛኛው በከብት እርባታ ላይ የተሠረተ መሆንና ለከብቶቻቸው ሰፊና ምቹ የግጦሽ መሬት ፍለጋ፣ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የሀዲያ ህዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይነትና ከሌሎች የሙስሊም ሱልጣኔቶች ጋር ትብብሩ እያደገ መምጣት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ጠንካራ የነበረው የክርስቲያኑ መንግሥት በመጀመሪያው እልፍ ዓመተ ምህረት መጨረሻዎቹ አካባቢዎች በተለይም በ9ኛውና 10ኛው ክፍለ ዘመን በውስጣዊና ውጫዊ ሃይሎችና ምክንያቶች ፈተና የገጠመው ወቅት ነበረ። በዚህ ተመሳሳይ ወቅት በአረቡ ዓለም ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠር የቻለው የእስልምና ሃይማኖት በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ ጠረፎችና ጠረፋማ አካባቢዎች መግባት የጀመረበት ጊዜ ነበር።

በርተን (1984) የተባሉት ጸሐፊ እንደገለጹት አረቦች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ጠረፋማ አካባቢዎች ይኖሩ ከነበሩት የሀዲያ ህዝብ ጋር ግንኙነት መፍጠር የጀመሩት በ7ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ጀምሮ ነበረ። በዚያን [illegible] የሀዲያ ህዝብ በቀይ ባህር ጠረፍና በሰሜኑ ከፍተኛ ቦታዎች መካከል በሚገኙት ረባዳማ ሥፍራዎች ይኖር ነበር። ስለዚህም አረቦች ከሀዲያ ህዝብ ጋር የመጀመሪያውን ግንኙነት የፈጠሩት የሀዲያ ህዝብ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ መንቀሳቀስ ከመጀመራቸው በፊት ነበር።





እነዚህ ግንኙነቶች የወደፊቱን የሀዲያ ህዝብና መንግሥት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይነት ሊወስኑ ችለዋል።

ኡለንዶርፍ (1966) እንደገለፀው በ9ኛው እና በ10ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግሥት መዳከም ጋር ተያይዞ የእስልምና ሃይማኖት በቀይ ባህር ጠረፍና በኢትዮጵያ የሰሜን ከፍተኛ ቦታዎች መካከል በሚኖሩ ከብት አርቢ ማህበረሰቦች ላይ ተፅዕኖውን ማጠናከር ችሏል። በመጨረሻም ከ10ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን መካከል ባሉት ወቅቶች የእስልምና ሃይማኖት ወደ ምሥራቅ ሸዋና ወደ ሲዳማ ሀገር ሊገባ ችሏል።

ኡለንዶርፍ (1966፡601) የተባለው ፀሐፊ በተመሳሳይ ሥራው የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት የሲዳማንና የጉራጌን አገር እንደሚያጠቃልል ይገልፃል። በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ዘመን የእስልምና ሃይማኖት የገባበት የሲዳማ ሀገር የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት አካል እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት

1ኛ፣ የአረብ ህዝብ ከሀዲያ ህዝብ ጋር ከእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት በፊትም ጀምሮ ግንኙነት ፈጥሮ የሚኖር መሆኑና

2ኛ፣ ከ10ኛው እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት በሀዲያ ውስጥ ተዋቂ ሀይማኖት መሆኑን በመውሰድ

ከ10ኛው እስከ 12ኛው ክፍል ዘመን ያለው ጊዜ የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት የተመሰረተበት ዘመንን የሚወክል እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል። ይህንን ግንዛቤ ሲያጠናክር የሚችለው የላጵሶ (2003) ግምት ነው። ላጵሶ እንደገለጸዉ የሀዲያንና ሌሎችም ለምሳሌ የይፋት፣ የሸዋ እስላማዊ መንግሥታት የተፈጠሩት (የተነሱት) በመጀመሪያ እልፍ አመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ በመጨረሻው ክፍል ዘመን (Century) እንደነበረ ይጠራጠራል። ከላይ ከተጠቀሰት እውነታዎች በተጨማሪ የሀዲያ ህዝብ ከአረቡ ዓለም ጋር ግንኙነት መመሥረት የጀመረበት ቦታ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ጫፍ ሲሆን የሀዲያ እስላማዊ መንግስት ምስረታ የተጠናቀቀው ግን ሀዲያ ወደ ደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል በተወሰነ ርቀት ከተንቀሰቀሰ በኋላ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ በሰሜን ኢትዮጵያ በራያ ማለትም በትግራይና በወሎ አካባቢዎች ለረጅም ዘመናት እንደኖረ መረዳት የሚቻል ሲሆን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ ለተወሰኑ ዘመናት በመሃል ኢትዮጵያ ከሚኖሩት የአገው ማኅበረሰቦች ጋር በመጎራበት ይኖር እንደነበረ የሀዲያ አፈ-ታሪክ ያወሳል።

## 2.3. የሀዲያ እስላማዊ መንግስት መገኛ

የሀዲያን እስላማዊ መንግሥት ጂኦግራፊያዊ ቦታውን የተለያዩ ፀሐፊዎች በተለያዩ መንገዶች ለማሳየት ጥረት አድርገዋል። የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም የበለጠ ሳይንሳዊና እርግጠኛ በመሆን (ለምሳሌ፣ ከአረብ ፀሐፊዎች አቡል ፊዳ)፣ ታዋቂ የሆኑ ወንዞችን፣ ሌሎች መንግሥታትንና ህዝቦችን መነሻ በማድረግ ወርዱንና ስፋቱን መግለፅ (አል ኡመሪና መቅሪፅ)፣ የሀዲያን እስላማዊ መንግሥት አንፃራዊ መገኛን መነሻ በማድረግና (ለምሳሌ ኢብን ሳይድ) እንዲሁም የሰውን እርምጃና ኪሎ ሜትርን መለኪያ በማድረግ ጥንታዊ መገኛን ለማሳየት ሞክረዋል።





"Takwimal- Buldan" ተክማዋል ቡልዳን በሚል የጂኦግራፊ ሥራው የሚታወቀው አቡል ፊዳ በ1321 ዓ.ም. እንደዘገበው የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ጂኦግራፊያዊ መገኛው በእርግጠኝነት በ7 ዲግሪ ሰሜን ኬክሮስና በ57 ዲግሪ 3 ደቂቃ ምሥራቅ ኬንትሮስ መካከል[14] እንደነበረ ገልጸዋል። ምንም እንኳን የመለኪያው መሥፈርት ባይገለፅም አል ኡመሪና አል መቅሪፅ የተባሉ ፀሐፊዎች የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ቁመቱ ሃያ ቀናት ወርዱ ደግሞ የዘጠኝ ቀናት የእግር ጉዞ የሚፈጅ እንደነበረ ገልፀዋል። ከላይ የተገለፀውን ግምት በማጠናከር አል ኡምሪ የሀዲያ እስላማዊ መንግሥትን ስፋት ሲያስረዳ ቁመቱ 160 ኪሎ ሜትር ፣ ጐኑ ደግሞ 172 ኪሎ ሜትር በመሆን በአጠቃለይ ስፋቱ 27,500 እስኩዌር ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ቦታ የያዘ እንደነበረ አስረድተዋል። ኢብን ሰይድ የተባለ ሌላ የአረብ ፀሐፊ የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት መገኛ ከይፋት እስላማዊ መንግሥት በስተደቡብ እንደሆነ ገልጿል። ይህንን ሀሳብ የሚጋራ የሀዲያን ህዝብ መገኛ የገለፀው ፍራንችስኮ አልቨሬዝ የተባለ የፓርቹጋል ተጓዥ እንዳመለከተው የሀዲያ አገር ከዋግና ከመካከለኛው አዳል እስከ ሞቃዲሾ ድረስ የተዘረጋ እንደነበረ አስታውቋል።

በጥቅሉ ምንም እንኳን የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት አገር (መገኛ) በተለያዩ መንገዶች በተለያዩ ፀሐፊዎች በተለያዩ ሰፋፊ ቦታዎች ቢጠቆምም በመካከለኛው የኢትዮጵያ የታሪክ ዘመን በአዋሽና በጊቤ ወንዞች መካከል የሚገኘውን ሰፊ መሬት ተቆጣጥሮ እንደነበረ መረዳት ይቻላል።

14 ይህ መገኛ ከዛሬዉ የሀድያ ዞን መገኛ 7° እና 45' ሰሜን 38° እና 28' ምስራቅ ጋር ይቀራረባል።

አብዛኞቹ የጽሁፍ ማስረጃዎች (ለምሳሌ ፣ትርምንግሃም 1952 ፣ ኡለንዶርፍ 1966) የሀዲያን እስላማዊ መንግሥት ከሁሉም የዘመኑ እስላማዊ መንግሥታት በምዕራባዊ ጫፍ ላይ በመገኘት በአባይና በጊቤ ወንዞች መካከል ያለውን ሰፊ መሬት ተቆጣጥሮ እንደነበረ ይስማማሉ፡፡ ፍራንችስኮ አልቫሬዝ የተባለውም በዘመኑ የነበረው ፖርቹጋላዊ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት በአዋሽና በግቤ ወንዞች መካከል እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡ ይሀው የፖርቹጋል ተጓዥ በመካከለኛ ዘመን የሀዲያ መንግሥት በደቡብ ጫፍ በኡልባራግ ወረዳ እንደሚዋሰንና የዝዋይ ሀይቅም በሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ክልል ውስጥ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

## 2.4. የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ከ13ኛ እስከ 17ኛ ክፍለ ዘመን

በክርስቲያኑ መንግሥት ምንጮች ስለ ሀዲያ ህዝብ መጻፍና መገለፅ እንደገና የተነቃቃው (revived) ለሰሞናዊ ሥርወ መንግሥት የተበለው ሀይል ወደ ሥልጣን ከመመለስ ጋር ተያይዞ ከ1270 ዓ.ም. ከክርስቶስ ልደት በኂላ ነበር፡፡ ሀበርለንድ (1964፡236) እንደጠቀሰው በመካከለኛው የኢትዮጵያ ክፍል ሠፍሮ የነበረው የሀዲያ ህዝብ ክብረ ነገሥት በተባለው የክርስቲያኑ መንግሥት መፅሐፍ ውስጥ የክርስቲያኑ መንግሥት ዘመናትን የተሻገሩ /Hereditary/ ጠላቶች ተብለው ተገልፅዋል፡፡ የሀዲያን ህዝብ ለክርስቲያኑ መንግሥት ዘመናትን የተሻገሩ ጠላቶች በሚል መገለፃቸው በሀዲያና በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እየተጠናከሩ በመጡት የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ሃይሎች መካከል ከአንጌቦ መንግሥት ዘመን ጀምሮ የነበረውን ግንኙነት ያመለክታል፡፡ ከዚሀ በተጨማሪ ክብረ ነገሥት ከመጻፉ በፊት የሀዲያ ህዝብና የሴም ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የሰሜን





ኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ መንግሥት ጐን ለጐን ለረጅም ዘመናት መኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡ ምክንያቱም የዘመኑን የቴክኖሎጂ ዕድገት ደረጃ ታሳቢ በማድረግ በእነዚህ ሁለቱ ሀይሎች መካከል ከዘር ዘር እየተላለፉ ዘመናትን የሚሻገር ቁርሾና ጠላትነት ሊኖር የሚችለው ኩታ ገጠም በሆነ አካባቢ የሚኖሩና ተቃራኒ የሆነ ፍላጐት ያላቸው ከሆነ ነው፡፡

ክብረ ነገሥት ውስጥ የተገለጸዉና ከክርስቲያኑ መንግሥት የዘመናት ጠላት ከሆኑት የሀዲያ ህዝብ ጋር ጦርነት በመግጠም ህዝቡንም ያሸነፈውና አገራቸውን ያጠፋው ንጉሥ ቀዳማዊ ምኒልክ ነው የተባለውም ቢያንስ ቢያንስ የጠላትነትና የጦርነቶች መነሻ ከክርስቶስ ልደት በፊት የመጀመሪያ ሚሊኒየም የመጀመሪያዎቹ አመታት ላይ በማመልከት ጠላትነቱ እጅግ ጥንትና ሩቅ ዘመን ጀምሮ የነበረ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

### 2.4.1. በሀዲያና በክርስቲያኑ የሰሜን ኢትዮጵያ መንግስት መካከል የነበረዉ በጦርነት ላይ ብቻ የተመሰረተዉ ግንኙነት

በሀዲያ እስላማዊ መንግሥትና በክርስቲያኑ መንግሥት መካከል የነበረው የጠላትነት ግንኙነት የከፋ ደረጃ በመድረስ ወደ አስከፊ ጦርነት የተለወጠው ንጉሥ አምደ ፅዩን (1314 – 1344) ዓ.ም. የክርስቲያኑን መንግሥት ዙፋን ከተቆጣጠረ በኂላ ነው፡፡

የሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ አምደፅዮን ወደ ሥልጣን እስከ መጣበት ጊዜ በተለይም ከይኩኖ አምላክ ስልጣን ማብቃት ቀጥሎ ያለው ዘመን (1385 – 1314) ዓ.ም. በክርስቲያኑ መንግስት ውስጥ በነበረው የሥልጣን እሽቅድምድም ስርዓቱ በውስጥ ችግሮች የተሽመደመደበት ጠቅት ነበረ፡፡

በ1314 ዓ.ም. አምደፅዮን ወደ ሥልጣን እንደመጣ የራሱን መንግሥት ውስጣዊ ችግሮች መፍታትን ለጊዜው በማቆየት በሀዲያ፣ በዳሞትና በጉጃም መንግሥትታት ላይ ዘመቻ አካሄደ። አምደፅዮን በታደሰ (1972፡135) እንደተገለፀው በሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ላይ የመጀመሪያውን ዘመቻ ያካሄደው በ1316/ 1317 ዓ.ም. ከክርስቶስ ልደት በኋላ ነበረ።

በዚህ ዘመቻ አምደጽዮን በሀድያ ህዝብ ላይ ያደረሰዉን ግፍ ታደሰ (1972፣ 106) እንደምከተለዉ ጽፏል።

> *አምደጽዮን በዚህ አገር [በሀዲያ] ሰዎች ላይ ታላቅ ጭፍጨፋ ፈጸመ፣ አንዳንዶቹን በሰይፍ በማረድ፣ አንዳንዶቹን ደግሞ ከንጉሳቸዉ ጋር ታላቅ፣ ታናሽ፣ ወንድ፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ወጣት ወደ ራሱ መንግስት በምርኮ በመዉሰድ*

ንጉሥ አምደፅዮን ይህን የሀዲያ ላይ ዘመቻ ያደረገው በዘመኑ የክርስቲያኑ መንግሥት ደቡባዊ ወረዳ በነበረው በአይመለል በኩል በማድረግ ነበረ። በመጀመሪያው የሀዲያ ዘመቻ ያገኘውን ድል በማስመልከት ንጉሥ አምደፅዮን አምላኩን ሲያመሰግን የተነገረውን ቃል ታደሰ (1972፡135) እንደሚከተለው አስቀምጧል።

> *በ1316/1317 ዓ.ም. ከክርስቶስ ልደት በኋላ የቅዱስ እስጢፋኖስንና የአባቴን የክርስቶስ ተስፋና ፀሎት በማመን (trusting) ወደ ጦርነት ሄድኩኝ። እናም አምላክ የሀዲያን ህዝብ ሁሉ ወንዱንም ሴቱንም ከቁጥር በላይ አሳልፎ ሰጠኝ። ህዝቡን ወደ ሌላ ቦታ በስደት ወሰድኳቸው።*



*የሀዲያ ህዝብ ታሪክና ባህል*

በመጀመሪያው የሀዲያና የአምደፅዮን ጦርነት ወቅት የሀዲያ መሪ ነበረ ተብሎ የሚታመነው አመኖ የሚባል ሰው ነው። በዘመኑ በነበረው ልማድ መሠረት አመኖ ከተሸነፈ በኋላ በምርኮኝነት በክርስቲያኑ መንግሥት እንደተወሰደ ይገልፃል። የሀዲያ ንጉሥ የተወሰደበትንም ምክንያት ታደሰ (1972፡ 106) ሲገልጽ ህዝቡና (የሀዲያ ህዝብ) ዘመዶቹ መልካም ባህርይ እንዲያሳዩ እንደ መያዣ (hostage) ተደርጐ ነው ይላል። ይህ በዘመኑ የነበረውና በተሸናፊ ህዝቦች መሪዎች ላይ የሚወሰድ እርምጃ[15] ነበረ።

ነገር ግን ዶናልድ ሌቪን (1993፡15) የተባለ ፀሐፊ፣ አመኖ የሚለው ቃል የሰው ሥም ሳይሆን የማዕረግ ስም እንደሆነ ይገልፃል። ጸሃፊው ለዚህ ሀሳቡ እንደ ምክንያት ያቀረበው አመኖ የሚለው ቃል ከአንድ ዘመን በኋላም በዘርአ ያዕቆብ ዜማ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል የሚል ነው። ብራውካምፐር የተባለውም ፀሐፊ በተመሳሳይ መልኩ አመኖ የማዕረግ ሥም እንደሆነ ሲያስረዳ እንደምክንያት ያስቀመጠው በሀዲያ የዘር ሀረግ ቆጠራ አመኖ የሚል ቅድመ አያት አለመጠቀሱን ነው። ነገር ግን አመኖ የሚለው ቃል በተለያዩና በተራራቁ ዘመናት ተደጋግሞ መገለፁ ብቻውን ቃሉን የሰው ሥም ሳይሆን የማዕረግ ሥም ነው ብሎ ለመከራከር በቂ መረጃ ሊሆን የሚችል አይመስልም። አመኖ በሀዲያ አፈ ታሪክ መሠረትና በዚህም ዘመን በሀዲያ ህዝብ ዘንድ ከተለመዱት ስሞች አመዕኖ /Amma'nno/ የሚለውን ሥም ይወክላል ተብሎ ይታመናል። የስሙ በተራራቁ

[15] በተሸናፊ ህዝቦች መሪዎች ላይ በመካከለኛዉ የኢትዮጵያ ታሪክ ዘመን በክርስቲያኑ መንግስት ይወሰድ ስለነበረዉ እርምጃ ታደሰ (1972፣ 106) ሲያስረዳ በመጀመሪያ ተሸናፊ መሪዎች ህዝባቸዉና ዘመዶቻቸዉ መልካም በሀሪይ እንዲያሳዩ እንደ መያዣ እቤተመንግስት ይቀመጣሉ።የተሃድሶ ጊዜ ሲያበቃ እነዚሁ የተሸናፊ ህዝብ መሪዎች ተመልሰዉ ህዝባቸዉን ለማስተዳደር ተመራጭ ይሆናሉ።

ዘመናት ተደጋግሞ መከሰት ይህ ስም በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅና ጥሩ ትርጉም ያለው መሆኑን ብቻ ያመለክታል፡፡

አመኖ የሚለውን ቃል የሀዲያ መሪ ሥም ነው ብለን በመውሰድ መሪው በክርስቲያኑ መንግሥት ለተወሰነ ጊዜ እንደመያዣ ተይዞ ከቆየ በኋላ የክርስቲያኑ መንግሥት በሀዲያ ህዝብ ላይ ያለው አመኔታ ሲጠናከር አመኖ እንደገና ተመልሶ ህዝቡን እንዳስተዳደረ ይገመታል፡፡ ነገር ግን ስለ አመኖ ተመልሶ ማስተዳደር ከዘመኑ ተለምዶ ተነስቶ ከመገመት ውጪ በአምደ ጽዮን ዜና መዋዕል ላይ ምንም የተገለፀ ነገር የለም፡፡

ከ1316/17 የንጉሥ አምደፅዮን የሀዲያ ጦርነት በኋላ ሠላማዊ ግንኙነት ቢቀጥልም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሀዲያ ህዝብ ክክርስቲያኑ የአምደፅዮን መንግሥት ጋር የነበረው ሰላማዊ ግንኙነት ተመልሶ መበላሸት ጀምሯል፡፡ ለግንኙነት መበላሸትና ለዳግም አመፅ መነሻ ነው የሚባለውን ነገር የአምደ ጽዮን ዜና መዋእል ሲያስረዳ "የውሸት ነብይ" /False Prophet / ትምህርትና ግፊት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ አመኖ በታደሰ (1972 ፤136)፣ በብራውካምፔር (1973) እና በብራውካምፔር (2004፣ 54) እንደተገለፀው በውሸት ነብይ ትምህርት በመገፋፋት ወደ ንጉሱ ቤተ መንግሥት መምጣትና የተለመደውን ግብር መክፈል በማቆም አመፅ ጀመረ፡፡ ይህንን ሁኔታ የአምደፅዮንን ዜና መዋዕል እንደ ዋቢ በመጠቀም ተስፋዬ (1993፡ 34) እንደሚከተለው ጠቅሷል፡፡





*የሀዲያ ህዝብ አልገብርም ብሎ ከመሸፈቱም በላይ ሰብረአዲን የተባለው የዘይላ እስላማዊ ክፍለ ግዛት (ባሌ፣ ሸርሃ፣ ደራ፣ ይፋት፣ አረባብኒ፣ ደዋሮ) ዋና መሪ ጋር በማበርና አማኖ ወይም አሚኖ ... አበጋዝነት በአፄው መዕከላዊ መንግሥት ላይ ጦርነት ስለከፈተ አፄ አምደጽዮን በ1321 ዓ.ም. ከእስላሞች ጋር ከፍተኛ ጦርነት አድርጎ ብዙ ህዝብ እንደፈጀና ብዙውንም ህዝብ እንደማረከ በዜና መዋዕሉ ሲገልፅ ... ይህ ከፋ ሰው (ሰብረ አዲን) ከዚያ በኋላ ትንቢት ተናጋሪዎችን ጠየቃቸው፣ እንዲህ ሲል፣ "አሁን እስቲ ንገሩኝ፣ እለምናችኋለሁ፣ ከክርስቲያኖች ንጉሥ ጋር ጦርነት ብንከፍት ለማሸነፍ እንችላለን?" ከእነርሱ መካከል አንዱ ተነሣ፣ እንደበልዓም የጨለመ ነብይ የሆነና ቀደም ሲል እምኖ የተባለውን የሀዲያ ንጉሥ እንዲህ ሲል ያሳሳተና ያምበረበረ፣"ወደ ጽዮን ንጉሥ አትሂድ፣ ስጦታና ግብርም አትስጠው፣ እርሱ አንተን ሊወጋ ከመጣብህ አትፍራው፣ እርሱ በአንተ እጅ ይወድቃል፣ እርሱና ሠራዊቱም በአንተ እጅ ይደመሰሳሉ፡፡" እነዚህም የውሸታም /የሐሰተኛ/ ነብይ ቃላትን የሀዲያው ንጉሥ አማኖ በመተማመን በፅዮን ንጉሥ ላይ አመጸ፡፡ ነገር ግን እንደሳምሶን ሃያል፣ እንደዳዊት ታላቅ ጦረኛ (ጀግና)፣ በጦርነት ድል አድራጊና ራሱም ተሸንፎ የማያውቅ ንጉሥ አምደ ፅዮን በቁጣ ተነሳ፣ ወደ ሀዲያ ምድርም ዘመተ ፤ የአገሩንም ነዋሪዎች በሰይፍ ጨረሳቸው፣ ገሚሱንም ደመሰሰ፣ ገሚሱንም ከነንጉሳቸው ማረካቸው፣ አሮጊቶችንና ሽማግሌዎችን፣ ወጣቶቻቸውን፣ ወንዶችን፣ ሴቶችንና ልጆችን ሁሉንም በምርኮ ወደ ዋና ከተማው አመጣቸው፣ ያም ሐሰተኛ ነብይ ሸሽቶ ወደ ይፋት ግዛት ገባ፡፡*

ወደ ይፋት ሸሽቶ የገባው "ሐሰተኛ ነብይ" እዚያም በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ አመፅ እንዲቀሰቀስ ምክንያት እንደሆነ ተገልፆአል፡፡

ስለ ሀሰተኛ ነብይ በንጉስ አምደ ጽዮን መዋእለ ንዋይ የተገለጸዉን ሀይሌ (1971፡2) ሲያብራሩ የሀዲያ ንጉስ እሸዋን በመጠቀምና ጸሃይን፣ ጨረቃንና ኰዋክብትን በመመልከት ወይንም በማጥናት

ትንቢት በሚናገረዉ ሰዉ ተመክሮ ለንጉሱ አልገብርም ማለቱን ገልጿል፡፡ይህ ሀሰተኛ ነብይ ይባል የነበረዉን ሀይሌ (ዝኒ ከማሁ:2) የሀዲያን አንጃማ /Anjaamma/[16] ሲወክል እንደሚችል ይጠቁማል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጦርነት መጨረሻ ላይ የክርስቲያኑ መንግሥት ድል እንዳደረገ በአምደፅዮን ዜና መዋዕል የተገለፀ ሲሆን ንጉሥ አምደፅዮንም በሀዲያ ህዝብ ላይ አዲስ አቅጣጫ መከተላቸው ይታወቃል፡፡ በጦርነቱ ማብቂያ የአምደፅዮን አዲሱን ፕሮጀክት ታደሰ (1972፡91) ሲገልጽ ንጉሱ በሠራዊቱ አደረጃጀት ውስጥ አዲስ የሀዲያ ሠራዊት በማዋቀር በማዕከላዊው መንግሥት ሠራዊት ውስጥ አንድ የሀዲያ ክፍለ ጦር አደራጅቷል ይላል፡፡

እላይ በዝርዝር እንደተመለከተው በአምደፅዮን ዘመን የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት በአንድ ወቅት ለክርስቲያኑ መንግሥት በመገበር በሌላ ጊዜ ደግሞ በማመጽና ጦርነት በመግጠም ለክርስቲያኑ የአምደፅዮን መንግሥት ራስ ምታት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ብራውክምፔር (1980፡ 429) በአምደ ፅዮን ዘመን የነበረውን የሀዲያን መንግሥት አቋም ሲገልፅ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ምንም እንኳን ለተወሰኑ ጊዜያት በአምደ ፅዮን በመወረር ግብር ለክርስቲያኑ መንግሥት ቢከፍልም የራሱን ፖለቲካዊ ነፃነት አስጠብቆ ቆይቷል ይላል፡፡

በ14ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የንግድ እንቅስቃሴ ሀዲያ የነበረውን ሚና የአረብ ፀሐፊዎች ከባሪያ ንግድ ጋር አያይዘው ገልፀዋል፡፡

[16] አንጃማ /Anjaamma/ በአብዛኛዉ የሀዲያ አካባቢ የፋንዳኖ /Fandaano/ እምነት መሪዎችን ሲወክል በባደዋቾ /Baadawwacho/ የዶድች መና / Dooddichch manna/ ጎሳ መሪ ዛሬም አንጃንቾ ተብሎ ይጠራል፡፡





በተለይም ሀዲያ በአምደፅዮን እንደገና ከተያዘ በኋላ ወደ መካከለኛው ምሥራቅና ወደ ሰሜን አፍሪካ በሚደረገው የባሪያ ንግድ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ችግር መፈጠሩ ይገለፃል፡፡ ከባሪያ ንግድ ጋር ተያይዞ የሀዲያ አገር ዋስል ከተባለው ቦታ ተሰልበው የሚመጡ ባሪያዎች የህክምና እርዳታና መድሃኒት በሀዲያ ባህላዊ ሀኪሞች (ጭራሳ /Cireessa/) ተደርጉላቸው ቁስላቸው ከዳነ በኋላ ወደ ዉጪ በተለይም ወደ ግብፅ ለመላክ የሚዘጋጅበት ቦታ እንደነበረ አል ኡመርን በመጥቀስ ተስፋዬ (1993) ገልጿል፡፡

የዚህ ዋስል[17] ወይም ዋሽሎ ተብሎ የሚጠራው ባሪያዎች የሚሰለቡበትና መልካቸው የሚቀየርበት ቦታ ትክክለኛው መገኛው አከራካሪ ቢሆንም በሀዲያ አገር ውስጥ እንዳልነበረ ግን ግልፅ ነው፡፡

ከአምደ ፅዮን ዘመን በኋላም የተነሱት የክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት ለምሳሌ አጼ ዳዊት 1ኛዉ (1382-1413) እና ይስሃቅ (1414-1429) ከአካባቢው እስላማዊ ሱልጣኔቶች ጋር የማያቋርጥና ደም አፋሳሽ ጦርነቶችን አካሂደዋል፡፡ ምንም እንኳን ግንኙነቱ ሰላማዊ ባይሆንም የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት እስከ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ድረስ ለክርስቲያኑ መንግሥት ግብር እየከፈለ ቆይቷል፡፡ በዘርዓ ያዕቆብ ዜና መዋዕል እንደተገለፈው የሀዲያው ንጉሥ ገራድ /Garaad/ ማሒቆ (ማሂኮ) /የገራድ መሐመድ ልጅ የነበረው/ ለክርስቲያኑ መንግሥት አልገብርም

[17] አብን ሰይድ የተባለ የአረብ ጸሃፊ የቦታዉን ስም ሳይጠቅስ በሀዲያ አጠገብ የሚገኝ መንደር ሲለዉ ስሙን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመዉ ግን አል- ኡመር ነዉ፡፡ ቦታዉ ምንአልባትም ከሀዲያ በስተደቡብ የሚገኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ፋቱህ አል ሀበሻ ላይ አረብ ፋቅህ የተባለ ጸሀፊ ዋሽሉህ በማለት ከሀዲያ በደቡብ ምዕራብ በገንዝ ጥግ ይገኛል ያለዉ ቦታ ከሁሉም የተሻለ ከዋስል ጋር ይቀራረባል (ታደሰ 1972፣ 86)፡፡

ብሎ በማመፅ ለጦርነት ተዘጋጀ። በጦርነቱም ላይ የክርስቲያኑን መንግሥት ለማሸነፍ እንዲቻል በወቅቱ የእስላሞች ክፍል ግዛት (empire) መሪ ከነበረው የአዳል መንግሥት መሪ ጋር የትብብር ስምምነት ለመፍጠር ሞከረ።

ነገር ግን የሀዲያ ገራድ የነበረው ማኢቆ የክርስቲያኑ መንግሥት በጦርነት ለማሸነፍ ያቀደውን ዕቅድ ሌላው የሀዲያ መሪ የጋዳያቶ ገራድ ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ በማጋለጥ ጦርነቱን ለማሸነፍ የሚያስችል አዲስ ስልት ጠቆመ። በአዲሱም ሀሳብ መሠረት የሀዲያ እስላማዊ መንግሥትን ገራድነት ለአፄው ታማኝ ለሆነው ለጋረድ ባሞ /Baamo/ እንዲሰጥና አማፂውን ቡድን እሱ እንዲወጋው ታቀደ።

በዚህም ሀሳብ መሠረት ገራድ ባሞ ወደ ደብረብርሃን ወደ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቤተ መንግሥት ተጠርቶ አስፈላጊው ምክክርና ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የሀዲያ ህዝብ አፈ ታሪክን በመጥቀስ ብራውካምፔር (1989፡ 17) እንደዛፈው ባሞ በዚህ ስምምነት ወቅት የመሪነትና የሥልጣን ምልክት የሆነውን ቀይ ልብስ (ቀይ ጃኖ) በዘርዓ ያዕቆብ ተበረከተለት። ከዚያም በተጨማሪ በጦርነቱ የክርስቲያኑ መንግሥት ስጋት የሆነው ማኢቆን እንዲያሸንፍ በማሰብ ከዳሞት መንግሥት የተዉጣጣ ምርጥ ሠራዊት እንደተሰጠው ይገለፃል። የክርስቲያኑ መንግሥት የባሞን ታማኝነት ለማረጋገጥ በርካታ ሥጦታዎችን ጭምር እንደሰጠው በአፄው ዜና መዋዕል ተፅፏል።

በዚህ ወቅት የማኢቆ አመፅ ተባባሪ የነበሩት የሀዲያ ገራዶች መካከል የጉዳላ፣ የዲሆ፣ የሃይባ፣ የገንዝ፣ የሰጋ፣ የገደብ፣ የቀቤና፣ የጉጋላ ወይም የዶዶላ፣እና የሐላባ ገራዶች ዋናዎቹ እንደነበሩ ተጠቅሷል (ተስፋዬ 1993፣ 36)። በገራድ ማኢቆ በሚመሩት የሀዲያ ሀይሎችና በገራድ ባሞ የሚመሩት





የሀዲያ እና የዳሞት የክርስቲያኑ መንግሥት ደጋፊ ሃይሎች መካከል በተደረገው ጦርነት አብዛኞቹ የማኢቆ ደጋፊዎች ተሸንፈው እጃቸውን ሲሰጡ ገራድ ማኢቆ ከተወሰኑት ተዋጊዎች ጋር በመሆን ወደ አዳል አገር ለመሸሽ ሞክሯል። ነገር ግን የገራድ ባሞ ተዋጊዎች በሽሽት ላይ የነበሩትን ገራድ ማኢቆንና የሱን ተከታዮች አሳድደው እንደገደሏቸው ተጽፏል።

ከድሉ በኋላ በባሞ የተመራው የሀዲያ ሀይል ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ በርካታ ስጦታዎች እንደተበረከተለት ልዩ ክብርም እንደተሰጠው ተጠቅሷል። ከዳሞት የተውጣጣውና በሀዲያ መካከል በተደረገው የእርስ በርስ ጦርነት የተሳተፉት የክርስቲያኑ መንግሥት ምልምል ወታደሮች በሀዲያ አገር መሬት ተሰጥቷቸው እንዲሰፍሩ ተደርገዋል። ምንም እንኳን እነዚህ የውጪ ሀይሎች መሬት የተሰጣቸውና በሀዲያ አገር የሰፈሩት ለድሉ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ማካካሻ እንዲሆን ነው ቢባልም በተግባር ግን የሚመስለው ቀጣይ በገራድ ማኢቆ ደጋፊዎች ሊቀሰቀስ የሚችለውን አመፅ ለመከላከል ነው። ይህ በሀዲያ አገር የሰፈረው ምሪተኛ ሠራዊት (የዳሞት ወታደሮች) "ጨዋ" በሚባለው የጅምላ ስም ሲጠሩ የዳሞት ወታደሮች ሰፈር "በፀር ሾተል" ተብሎ ይታወቃል።

## 2.4.2.የጋብቻ ዝምድና በአማራጭነት መወሰዱ እና የንግስት እሌኒ ታላቅ ሚና

የክርስቲያኑ መንግሥት ከላይ የተገለፀውን ጦርነት፣ ስጦታና፣ የውጪ ሃይሎች ሠፈራ በሀዲያ አገር ላይ ቢያደርግም ከሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ጋር የነበረው ግንኙነት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊሻሻል አልቻለም። ከላይ ከተገለፁት እርምጃዎች በተጨማሪ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በሀዲያ እንቢተኛ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት እንዲያስችለው የሀዲያውን መሪ

የገራድ መሐመድን ሴት ልጅ በክርስትና እምነት አስጠምቆ ስሟን እሌኒ ስመ መንግስቷን ዣንዘላ (የዘይላ ንግሥት) በማሰኘት የቀኝ ባለቤት "ቀኝ *በአልቴሐቻ*" ወይም በሲቢዶ አፈታሪክ "ቀነኒ ባልቴት" ማዕረግ ሰጥቷት እንዳገባት በታሪክ ተፅፏል፡፡ ይህ የጋብቻ ዝምድናም በአፄ ዘርዓ ያዕቆብና በሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት መካከል ያለውን ግንኙነት ሊያሻሽል አልቻለም፡፡ እንዲያውም የቀነኒ ባልቴት (እሌኒ) አባት ገራድ መሐመድ ምንም እንኳን የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ አማች ቢሆኑም ሙስሊምና ሀዲያ በመሆናቸው በክርስቲያኑ መንግሥት ዘንድ ሊታመኑ እንዳልቻሉ ተጠቅሷል፡፡ ይህም በመሆኑ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የገራድ መሐመድን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በተለይም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በአንክሮ ይከታተል ነበረ፡፡

እሌኒን በተመለከተ በሚፃፉት የተለያዩ ፅሑፎች ስለ ማንነቷ የተወሰነ አለመግባባት ቢኖርም በክርስቲያኑ መንግሥት ውስጥ ስለነበራት ታላቅ ሚና ግን ሁሉም ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያራምዳሉ፡፡

የንግሥት እሌኒን ማንነት በተመለከተ ለምሳሌ፣ ይልማ (1966፡21)፣ ንግሥት እሌኒ አባቷ ገራድ አህመድ *(መሃመድ የሚለዉን የአባቷን ስም በስህተት የፃፉት ይመስላል)* የተባለ የደዋሮ ገዥ የነበረ ሰው መሆኑን ገልጿል፡፡ የጋብቻዋን ሁኔታና በክርስቲያኑ መንግሥት ስለነበራት ፖለቲካዊ ሚናዋም ይልማ (1966) ሲያብራራ ንግሥት እሌኒ አፄ ባዕደማሪያምን አግብታ ለእቴጌነት ማዕረግ መብቃቷን በመግለፅ ባሏ ባዕደ ማርያም በሞተ ጊዜ የንግሥት እሌኒ ዕድሜ በ25 እና በ30 ዓመት መካከል እንደሚገመት ፅፏል፡፡ ነገር ግን በባዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት በመንግሥት ጉዳይ ውስጥ እጅግም እንዳልተሳተፈች ተገልጿል፡፡ ይልማ (1966) እንደገለጸው





ንግሥት እሌኒ በደግነትና በሃይማኖታዊነት ረገድ ብርቱ ሴት መሆኗ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተገለጠ ስለሄደ በባልዋና በመንግሥት ሹማምንቶች ፊት ሞገስ ያላት ሆና ጠባይዋና አስተያየቷ ለከፍተኛ ተግባር የሚያሳጫት ሆኖ ስለተገኘ በተከታዮቹ በሁለቱ ነገሥታት ዘመን ማለትም በአፄ እስክንድርና በአፄ ያዕቆብ ሕፃንነት ዘመን የእንደራሴ ያህል ሆና የመንግሥቱን ሥራ ትመራ ነበረ፡፡

በ15ኛው ክፍለ ዘመን በክርስቲያኑ መንግሥትና በሙስሊም ሱልጣኔቶች መካከል የነበረውን ጠንካራ አለመግባባት በጦርነትና በሀይል ብቻ መፍታት አስቸጋሪ መሆኑን በመረዳት የክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት ሌላ የሚያግባባና ሰላም ሊያወርድ የሚችል ዘዴ መፈለግ ነበረባቸው፡፡ ስለዚህ አዲስ አስተሳሰብ አስፈላጊነትና ስለተወሰደ አዲስ አማራጭ ተክለፃድቅ (1968፡21) ሲያብራራ የክርስቲያኑ መንግሥት ያደረጋቸውን የጦርነት ጥረቶች በመጥቀስ ወረው ከተመለሱ በኋላ ተወራሪው እያንሰራራ ደግሞ ተመልሶ ስለሚመጣ ዘለቄታ ያለዉ ሰላም እንዲመሠረት በጦርነትና በወራረው ፈንታ ሌላ ሰላማዊ መንገድ ይፈልጉ ነበረ ብሏል፡፡

ይኸውም አዲስ ዘዴ ከሐድራሞት፣ ከሀዲያ፣ ከየመን እያፈለቁ መጥተው ለሀረርና ለአዳል ባላባትና መሪ ከሆኑት ዘር ውስጥ በጋብቻ የደመኝነትን ቁስል አድርቆ ዝምድናን መመስረት እንደ አማራጭ መወሰዱን ያወሳል፡፡ የዚህ አዲስ የግንኙነት እስትራቴጂን ውጤት ተክለ ፃድቅ (1968) ሲገልፅ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከሀዲያ ባለባት የምትወለደውን ጽዮን ሞጋሳ[18]

[18] ይህ ስም ለንግስት እሌኒ በቤተ- መንግስት ከተሰጧት ስሞች አንዱ ይመስላል፡፡

የምትባለዋን ሴት አግብተው ነበረ። እንዲሁም ልጃቸው ባአደ ማርያም እሌኒንና ሮማነ ወርቅን ሁለቱንም ከአዳል ባላባት የሚወለዱትን አግብተዉ እንደነበረ በመግለፅ እቴጌ እሌኒም ከአፄ ባእደ ማርያም ጀምሮ እስከ አፄ ልብነ ድንግል ድረስ ባለሥልጣን ሆነው የሠሩ መሆናቸው ተመልክቷል።

ከላይ የተገለጸውን የክርስቲያኑን መንግሥትና የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔትን የጋብቻ ዝምድናን ተክለ ፃድቅ (1993፡431) እንደሚከተለው አብራርቷል።

> *የሀዲያውን ባለባት የእምደ ጽዮን የጦርነት ታሪክ የሀዲያ ንጉሥ ሲለው የቀረው ሁሉ ዜና መዋዕል የሀድያ ገረድ ነው የሚለው። እርሱንም በጋብቻ ዝምድና ለመያዝ ሲሉ ነገስታቱ ሴት ልጆቹን ወስደው በክርስቲና ካስጠመቁ በኋላ ስማቸውን እሌኒ እያሰኙ ያገቡዋቸዋል። ... በዚህ መሠረት አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመናቸው የሀዲያውን የገረድ መሐመድን ልጅ አግብተው እሌኒ ቀኝ ባእልቴሐት (የቀኝ ባለቤት) አሠኝተው አግብተዋቸው ነበረ። ... ልጃቸው አፄ ባእደማርያም የዳዋሮውን ባላባት የመሐመድን ልጅ አግብተው እንደ አባታቸው እሌኒ ቀኝ በእልቴሐት አሰኝተው አግብተው ነበረ።*

እንግዲህ ከላይ የተገለጹት ፀሐፊዎች ካስቀመጧቸው ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ምናልባትም እሌኒ ከማንኛውም እስለማዊ ሱልጣኔት የክርስቲያኑ መንግሥት ነገሥታት የጦርነት ግንኙነትን ለማሻሻል ለሚያገቧቸው ሴቶች የሚሰጥ የክርስቲና ስም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ከሀዲያም ከዳዋሮም ከአዳልም በ15ኛው ክፍለ ዘመን የክርስቲያኑን መንግሥት ነገሥታት አገቡ የተባሉና እስላም መነሻ





የነበራቸዉ ሴቶች እሌኒ መባላቸውን ከላይ የተገለጹት ፅሁፎች ይጠቁማሉ (ይልማ 1966፣ ተክለ ፃድቅ 1968፣ ተክለፃድቅ 1993) ።

እሌኒ የሚለውን የክርስቲና ሥም ምናልባት ከላይ በተገለፀው ሁኔታ መረዳት ቢቻልም መሠረታዊው ጉዳይ በኢትዮጵያ የክርስቲያኑ መንግሥት ታሪክ ትልቁን ሚና የተጫወተችው የሀዲያው ገራድ የመሐመድ ልጅ የነበረችውና የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሚስት የነበረችው እሌኒ[19] እንደሆነች የዘመኑ ታሪክ ታላቅ ሲቅ ታደሰ (1972፡ 287-290) በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ አብራርቷል። ሁኔታውን ታደሰ (1972፡288) እንደሚከተለው ፅፏል።

> *... እሌኒ በመሠረቱ ከ1445 ማለትም ባዕደ ማርያም ከመወለዱ በፊት ጀምሮ የሀዲያ ተወላጅ የሆነች ልዕልት ናት። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲሞት ንግሥት እሌኒ የቀድሞ ማዕረጓ የነበረውን ቀኝ በአልቴሐትነት በተከታዩ ንጉሥም ዘመን ተጠብቆላታል። በአፄ ባዕደ ማርያም ዘመነ መንግሥት የእሌኒ ማዕረግ ስማዊ* (ceremonial) *ብቻ ሆኖ የዘለቀ ሲሆን ከንጉሱም አራት ሚስቶች[20] መካከል አትቆጠርም ነበረ። ንጉሡ ባዕደ ማርያም ዘውድ ከመጫኑ በፊት የራሱን እናት በሞት ያጣ ስለነበረ አዋቂዋና ብልጧ ንግሥት እሌኒ*

[19] Wikipedia, Free Encyclopedia ንግስት እሌኒንና ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን የሀዲያ ዝነኛ (famous) ግለሰቦች ብሎ አስቀምጧቸዋል።

[20] አራቱ የንጉስ ባዕደ ማሪያም ሚስቶች የተባሉት ዣን-ሰይፈ፣ ዳዊት-ኤራ፣ ሮምና፣እና እሬሽ - ጋዜት ናቸዉ (ታደሰ 1972፡288)።

*የእናትነት ሚና ትጫወት ነበረ። የቀኝ በአልቴሕት ንግሥት እሌኒ በንጉሥ ባዕደ ማርያም ዘንድ እጅግ የተወደደች ነበረች። ምክንያቱም ንግሥቲቱ በሁሉም ነገር የተዋጣላት ነበረች። በመንፈሳዊ ጉዳዮች በመልካም ተግባሯና በጠንካራ እምነቷ፣ በፀሎትና በቁርባን ሁሉ የእግዚአብሔር ፊት በመፈለግ ትተጋ ነበረ። በዓለማዊ ጉዳዮችም ለነገሥታት መሶብ የሚመጥን ምግብ የማዘጋጀት ሙያዋ፣ የንባብ ልምዷና የመጽሐፍት እውቀቷ፣ የሕግ እውቀቷ እና የመንግሥት የተለያዩ ጉዳዮችን በመረዳት ችሎታዋ ተወዳዳሪ የማይገኝላት የተዋጣላት ሴት ነበረች። በዚህ ሁሉ ምክንያት ንጉሱ እሌኒን እጅግ ይወዳትም እንደራሱ እናት ይመለከታትም ነበረ።*

በመሆኑም የሀዲያው ገራድ የመሐመድ ልጅ የነበረችውን ንግሥት እሌኒ በክርስቲያኑ መንግሥት ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠር የቻለችውና እጅግ ታዋቂ የነበረችው በአፄ ባዕደማሪያም ዘመን መንግሥት ነበረ። ይህች እሌኒ የባዕደማርያም ሚስት እንዳልነበረች ነገር ግን ንጉሡ የቀኝ በዓልቴሐትነትን ማዕረግ እንዳከበረላት በዘመኑ የነበረው የዓይን እማኝ ፑርቱጋላዊው ፍራንችስኮ አልቫሬዝ መስክሯል።

የንግሥት እሌኒን ፖለቲካዊ ሚና በተመለከተ ይልማ (1966፡ 22) ሲያብራራ ንግስቷ የክርስቲያኑ መንግሥት የዉጭ ጉዳይ ፖለቲካ መሪ እንደነበረች ገልጿል። ይህንን ጠንካራ ሃላፊነት ከአጼ ባዕደማሪያም መማክርት መካከል እሌኒ እድትሸከም የተደረገበት ምክንያት (ዝኒ ከመሁ፣ 22) ሲዘረዝር የእሌኒን በእድሜና በአዕምሮ በሳልነትን ፣ በአገራችን ትምህርት በጣም የላቀች መሆኗንና በባሕርይዋም ብልህነትና ርጋታ ያላት





መሆኗን ጠቅሷል። ከዚህም በተጨማሪ የክርስቲያኑን መንግሥት በዙሪያው ከከበቡት ሱልጣኔቶች መሪዎች ጋር በቤተሰባዊ ዝምድና ምክንያት በሰፊው የምትቀራረብ ስለነበረች በይበልጥ ልታገለግል የምትችል እሷ መሆኗን አመልክቷል።

ይልማ (1966) በእድሜ ታላቅነቷንና ልምዷን እንደ ሃላፊነቱ ምንጭ መጥቀሱ ንግሥት እሌኒ የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሚስት እንደነበረች አመላካች ነው። የዘመኑን የክርስቲያኑን መንግሥት የውጭ ጉዳይን በተመለከተ ንግሥት እሌኒ ሶስት ዋና ዋና ሃላፊነቶች መወጣት ነበረባት። እነርሱንም ይልማ (1996፡ 22) በሚከተለው ሁኔታ ገልጿል።

*1. ከእስላሞች ጋር የሚደረገውን ውስጥ ውስጡን ያለውን መጐሻመጥ ለማስቀረትና ኅብረትና አንድነት እንዲመሠረት ለማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ለማከናወን፤*

*2. ከኢትዮጵያ ግዛት ውጪ ከሚገኙት አገሮች ጋር የቆየው ጉርብትና ፀንቶ እንዲኖር መስማሚያና መቀራረቢያ መንገድ መፈለግ፤*

*3. የኢትዮጵያን እስላሞች ተጠግቶ ሃይማኖትን በማስታከክ በዘዴ ሊስፋፋ የሚሞክረው የኢምፔሪያሊዝምን እርምጃ ለመቃወም የሚቻልበትን መንገድ ስለመከታተል ነበረ።*

ከላይ በዝርዝር ከተቀመጡት ተልዕኮዎች አንፃር ንግሥት እሌኒ በክርስቲያኑ መንግሥትና በአረቦች እንዲሁም በአዳል ሡልጣን መካከል ሰላም እንዲወርድ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። ከዚህም በተጨማሪ ንግስቲቷ የክርስቲያኑ መንግሥት ከዐረቦች ጋር የነበረው ግንኙነት በሰላማዊ

መንገድ እንዲመራ አድርጋለች። ይልማ (1966) የኢምፔሪያሊስቶች ዛቻ ብሰው ከገለጹት ችግር ለመዳን የሚቻልበትን ሁኔታ በማለብ ንግሥት እሌኒ ጠንካራ ድጋፍ የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ተረድታ ከፖርቱጋሎች ጋር ስለ ጦር ጓደኝነት ድርድር እንዲጀመር አድርጋለች።

ከፖርቱጋሎች ጋር ስለተመሰረተዉ ወዳጅነት አጀማመር ተክለ ፃድቅ (1968: 23) ሲገልፅ:-

> *... እነዚህ /ስምንት የሚሆኑ የውጪ አገር ሰዎች ፔድሮ ደ ኮርቢልሃምን ጨምሮ/ ለንጉሡ ወዳጅ ሆነው ለሕዝቡም የእጅ ሥራ እያስተማሩ በከበሬታ ተቀምጠው በነበረበት ጊዜ የፖርቱጋልን መንግሥት ታላቅነትና ክርስቲያንነት በየቀኑ ለንጉሡ ለአፄ ልብነ ድንግልና ለእቴጌ እሌኒ ይነግሮዋቸዉ ነበረ። በዚህም ምክንያት እቴጌይቱ ወደ ፖርቱጋል ንጉሥ የወዳጅነት ደብዳቤ[21] ልከው የመረዳዳት ዝምድናን ለመመሥረት አሰቡ። ደብዳቤውንም ከነሎቹ ውስጥ ማንኛው እንደሚወስድ ምርጫ ሲደረግ ምርጫው ማቴዎስ እሚባለው የአርመን ተወላጅ (ነጋዴ) ላይ ወደቀ ....*

[21] እሌኒ ለፖርቱጋሉ ንጉስ የፃፈችዉን ደብዳቤ ፍሬ ነገር ምናሰ (1997፧ 17) እንደሚከተለዉ ፅፏል። ...የተወደድከዉና እጅግም ክርስትያን የሆንከዉ የፖርቱጋል ንጉስ ...የካይሮዉ ሱልጣን በህንድ የነበሩት የአንተ መርከበኞችና የጦር ሰዎች ያደረሱበትን ጥቃት ለመበቀል ታላቅ ስራዊት እያደራጀ እንዳለ ሰማን...የእንደዚህ ዓይነት ጠላትን ጥቃት ለመከላከል ወደ ጠረፍ አከባቢ ብዙ ቁጥር ያሰዉን ነፍጠኛ ለመላክ ዝግጁ ሆነናል...እላይ ካልነዉ በተጨማሪ የምንመከርህ የእኛን ሃይል ከተደረባችሁ ለተቀደሰዉ ሃይማኖታችን ጠላት የሆኑትን ለማዉደም የሚያስችል ጥንካሬ እንደምኖረን ነዉ...ነገር ግን እኛ ባህር ላይ ሠራዊት ለማስቀመጥ የሚያስችል አቅም የለንም። በዚህም ምክንያት ፈጣሪ ምስጋና ይግበዉና በባህር ጦርነት ጠንካራ ከሆናችሁት ከእናንተ ጋር ወዳጅነት አስፈላጊያችን ነዉ። እናንተ ሺህ መርከብ ማስታጠቅ ብትፈልጉ ለዚህ ጉዳይ የሚያስፈልገዉን ምግብም ሆነ ማንኛዉንም ነገር በብዙ መጠን እናቀርባለን።





በአጠቃላይ ታደሰ (1972፥288) እንደጠቀሰው የንግሥት እሌኒንና የአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጋብቻ ፖለቲካዊ እንደነበረና የሀዲያዉ ገራድ የመሐመድ ልጅ የነበረችዉ የእሌኒ ጠንካራ ፖለቲካዊ ሚና እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመን ድረስ እንደዘለቀ የሚያጠራጥር አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ የደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል በዘመኑ በነበረው ፖለቲካ የነበረው አስፈላጊነት እየጨመረ መምጣት ጋብቻውን ተገቢ አድርጎታል። ምንም እንኳን ከእስላም ሱልጣኔቶች ሀዲያንም ጨምሮ ሌሎች ሴቶችም የክርስቲያኑን መንግስት ነገስታት ቢያገቡም የእሌኒን ያክል ታላቅ ፖለቲካዊ ሚና የተጫወቱ አልነበሩም። ንግስት እሌኒ ለክርስቲያኑ መንግስት ሕልውና በዘመኗ ታላቅ አስተዋፅዖ ብታበረክትም የሀዲያ ገራዶች ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር የነበራቸው የጋብቻ ግንኙነት በደስታና ዝምድናን በመፈለግ ስሜት የተመሰረተ እንዳልነበረ ይልቁንም በግድ የተቀበሉት እንደሆነ ለአህመድ ግራኝ መግለፃቸውን (ተክለፃድቅ 1993፥ 432-433 እና ታደሰ 1972፥ 288) ገልፀዋል። ንግስት እሌኒም በ1522 ዓ.ም. እንደሞተች ይገመታል።

ኤደሞ (1999) በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ውስጥ የነበረው ጦርነት የሀዲያን በባሞ መሪነት ለክርስቲያኑ መንግሥት ታማኝ መሆንና የክርስቲያኑን መንግሥት ጊዜያዊ ድል ሲገልፅ ሀዲያ በዚህች ወቅት ገባር ሊሆን የቻለው በሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባትና የሥልጣን ሽኩቻ መሆኑን አመልክቷል። ኤደሞ (1999) የገራድ መሐመድ ልጅ ገራድ ማሂቆን ወይም ማኢቆን የሊበዶን የዘር ቆጠራ አፈ-ታሪክ

መሠረት በማድረግ ገረድ "መንሱሮ" /Mansuuro/ ብሎ አስቀምጧል። ቀነኒ በልቴት ወይንም ንግሥት እሌኒም የቢመደ (የመሐመድ) ልጅና የመንሱሮ (የማኢቆ) እና የማዮ እህት መሆኗን ፅፏል።

ከአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በኋላም እስከ አፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ድረስ በክርስቲያኑ መንግሥትና በሀዲያና እስላማዊ ሱልጣኔት መካከል የነበረው ግንኙነት በጥርጣሬ በአለመተማመን የተመሠረተ ሆኖ ዘልቋል። ለምሳሌ በአፄ በዕደ ማሪያም ዘመን መንግሥት (1468-1478) የእስላማዊ የአዳል መንግሥት በተደጋጋሚ ያምፅና በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጦርነት ይከፋት እንደነበረ ሲታወቅ በታሪክ ተጠቅሰው ያሉትን በጦርነቶቹ ተሣትፈው የነበሩትን አንዳንድ ስሞችን በመመልከት ብረውካምፔር እንዳለው የሀዲያ ህዝብ በጦርነቶቹ ተሣትፎ እንደነበራቸው ማወቅ ይቻላል። ተስፋዬ (1993፤36) ቤክንጋሃምንና ሀንትንግፎርድን (1954) በመጥቀስ እንዳስቀመጠው አፄ ልብነ ድንግልም በስልጣን ዘመኑ ከሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማጠንከር የጋብቻ ዝምድናን እንደመሳሪያ ለመጠቀም ማቀዱን እንደሚከተለው ገልጿል።

> *አፄ ልብነ ድንግል ግንኙነቱን ለማጠንከር የሀዲያው ገራድ ሴት ልጅ ለማግባት ከሀገርዋ ካስመጣት በኋላ በገጣጣሚቷ የተነሳ እርሱ ከእርሱ ጋር መጋባትን ትቶ ለአንዱ ቢትወደድ እንደዳራት በወቅቱ በአፄው ቤት መንግሥት የተገኘው ፖርቱጋላዊ ፊራንቸስኮ አልቫሬዝ (1520-1526) አረጋግጧል።*

ይህዉ ተመሳሳይ ሃሳብ በተክለጻድቅ (1993፡ 432) በተመሳሳይ ሁኔታ ተገልጿል።





በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን በነበረው ታሪክ የተጠቀሰውና በሀዲያ ህዝብ መካከል የነበረው አለመግባባትና የእርስ በርስ ጦርነት በአፄ ልብነ ድንግል ዘመንም የህዝቡ ትልቅ ችግር እንደነበረ የሚጠቁም መረጃ በዘመኑ የአይን እማኝ በነበረ አልቫሬዝ በተባለ ፖርቹጋላዊ ፅፏል። አልቨሬዝን በመጥቀስ (ኤደሞ 1999፤ ክበሞ 2007 እና ተስፋዬ 1993) እንደጠቀሱት የአፄው (የአፄ ልብነ ድንግል) ብትወደድ ሚስት የሆነችው የሀዲያ ሴት እህት የሀዲያው እስላማዊ ሱልጣኔት መሪ ሚስት እንደነበረች በመግለፅ የበሏን ሥልጣን ወንድሞቹ ለመንጠቅ ከፍተኛ ችግር መፍጠራቸውን በተረዳች ጊዜ ወደ አፄ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት እርዳታ ፍለጋ አቀናች። ሴትዮዋም ወደ ንጉሥ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት በመጣችበት ወቅት በበቅሎና በእግር አጃቢዎች እንደተከተሏትና በትክክል ንግሥት እንደምትመስል ተጠቅሷል። ንግሥቷም በሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ውስጥ የተከሰተውን የሥልጣን ሽኩቻና አለመረጋጋት ጠቅሳ ከአፄ ልብነ ድንግል እርዳታ ጠየቀች።

በዚህ መሠረት በአዱሪጋዝ የሚመራ 15000 ሠራዊት በሀዲያ እስላማዊ መንግሥት ውስጥ የተቀሰቀሰውን የእርስ በርስ ጦርነት እንዲያስቆሙ በአፄ ልብነ ድንግል መላኩን ሲገልፅ የተላከው ሃይል ግን ጦርነቱን የመቆጣጠር አቅም እንዳልነበረው ተገልጿል። ይባስ ብሎም የሀዲያ ህዝብ በአፄ ልብነ ድንግልም ላይ በማመጽ ግብር መገበር በማቋረጡ በንጉሡ በራሱ የሚመራ ዘመቻ ወደ ሀዲያ እንደተደረገ የንጉሥ ልብነ ድንግል ዜና መዋዕል ያስረዳል።

## 2.4.3. የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት በክርስቲያን እስላም ጦርነት ወቅት (1531-1543)

ከ16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ቀጥሎ ያለው ዘመን በክርስቲያኑ መንግሥትና በእስላም ሱልጣኔቶች መካከል የነበረው ትግል በጣም የጠነከረበትና ከፍተኛውን ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነበረ። የዚህ ጠንካራ ትግል ማብቂያ የሆነውና ረጅም ዓመታት የፈጀው የጂሃድ ጦርነት በአህመድ ኢብን እብራሂም አልጋሃዚ ወይንም በቅፅል ስሙ ግራኝ መሪነት በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ድል መቀዳጀት የጀመረውም ከ1529 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ብራውካምፔር (1980) በዚህ በክርስቲያኑ መንግሥትና በእስላም ሱልጣኔቶች ጥምር ጦር መካከል በተደረገው ትግል የሀዲያን እስላማዊ ሱልጣኔት ሚና ሲገልፅ የሀዲያ ህዝብ የአዳሎችን ትግል በዋናነት በፈቃደኝነት በ1531 በመቀላቀልና ከአዳል የጦር መሪዎች ጋር የጋብቻ ዝምድናን በመፍጠር የክርስቲያኑ መንግስት የእስላሞቹን ጥቃት በወይና ደጋ ጦርነት ላይ እስከሚያከሽፍ ድረስ መዋጋቱን ገልጿል።

የሀዲያ እስላማዊ መንግሥት እንዴት ከአፄ ልብነ ድንግል ቁጥጥር ነጻ ወጥቶ የአዲሱን የእስልምና ሃይሎች እንደተቀላቀለ የግራኝ አህመድ ልዩ ፀሐፊ የነበረው ዐረብ ፈቂህ ሲገልፅ ግራኝ ወደ ሀዲያ አገር ያደረገው ዘመቻ አላማ በእማካሪዎች ግሬት ተቀይሮ በሀዲያ አካባቢ ያሉትን የክርስቲያን መንግሥት ደጋፊ ህዝቦችና አካባቢዎች የሀዲያን ጦር በመጠቀም ለመቆጣጠር እንደታቀደ ጽፏል። ሁኔታውንም ዐረብ ፋቂህን በመጥቀስ ተክለ ጻዲቅ እንደሚከተለው ጠቅሷል።





ነገር ግን እስላሞች በቂ ስንቅ የለንምና ሐይቁ /ዝዋይ ሐይቅ/ ይቅርብን ይልቅስ ወደ ሀዲያ እንሂድ ፣ የሀዲያ ሰዎችንም የሐይቁን ክርስቲያኖች ለማሸነፍ ይበቃሉ ብለው ስለመከሩት ሐይቁን ተወውና ወደ ሀዲያ ደረሰ። የሀዲያ ሹም ወደ ይማም መጣ። እርሱም ለአበሻው ንጉሥ የሚገብር እስላም ነው። በየዓመቱ እንደልማዱ አንዲት ወጣት ሴት ልጅ ለንጉሡ እየገበረ ወጣቲቱ በክርስትና ትጠመቃለች። ይህ የሀዲያ ሹም ጦሩን ይዞ ወደ ይማም መጣና እኔም እንደናንተው እስላም ነኝ ለፈቃዳችሁ እታዘዛለሁ ብሎ ተናገረ። አህመድም በደህና ተቀበለው፣ እርሱም እስላሞችን በደንብ አስተናገዳቸው። ይማም ለእርሱ የሚያምር ሽልማት ሸልሞ ከርሱ ጋር ለመጡት የአገር ሹማምንቶች ልብስ አደላቸው። ወዲያውም እናንተ እስላሞች ሆናችሁ ለአበሻው ንጉሥ ቆንጆ ልጃገረዳችሁን የምትገብሩት እንደምን ነው? ብሎ ጠየቃቸው "ከእኛ ይበልጥ ንጉሱ ኃይል ስለነበረው ይህንን እንድናደርግ አባቶቻችንን አስገድዶ፣ መከላከያ ስይፋም እንዳይዙ ሌጣውን እንጅ የተጫና ፈረስ ላይ እንዳንወጣ ተከልክለን እንኖራለን። በዚህ ላይ በየዓመቱ አንዲት ወጣት ልጅ እንድንገብር አስገድዶን እኛንም እንዳይገድለንና መስጊዶቻችንን እንዳያፈርስ በመፍራት እንገብራለን። የግብሩን ገንዘብና ወጣቲቱን የሚረከበዉ ሰው ሲመጣ ወደውጪ አውጥተን አካሏን አጥበን በጨርቅ ገንዘን በቃሬዛ አድርገን እንደሞተች ቆጥረን ስለ እርሷ ጸልየን እናስረክባለን። በዚህ ዓይነት አባቶቻችንና አያቶቻችን ሁሉ ያደርጉ ነበረ። አሁን ግን ልዑል እግዚአብሄር እስላሞችን አመጣልን፣ ጌታችን የነበረውን አበረራችሁ፣ ወታደሩንም ጨረሳችው፣ ከእንግዲህ ወዲያ ከእናንተ ጋር ሆነን እንዋጋቸዋለን ሊያስቃዩን አይችሉም ብለው መለሱለት። ይማምም "እይሂችሁ ኃይላችሁን ከእኛው ጋር ደርቡት አላቸውና እነሱም እሽ ብለውት ከነርሱ አገር አምስት ቀን ከተቀመጠ በኋላ የሀዲያውን ሹም (መሪ) እንደያዘ ከሀዲያ ወደ አይፈረስ ሄዶ ተቀመጠ። የሀዲያው ገራድ በዚህ በእስላምነቱ [በሙስሊምነቱ] ምክንያት ለግራኝ እንደገባ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ሴት ልጁን ሙሪያስ የምትባለው ለአሸናፊው ለግራኝ አህመድ፣ እህቱን ለታማኙ ለአብዲ

> *ኢን ናስር በመዳር ዝምድናውን አጠናከረ። ከዚህ በኋላ ለግራኝ ፊጽሞ ታማኝ አገልጋዩ በመሆን ከእህቱ ባል ከአማቹ ከአብዲ ኢን ናስር ጋር ሆኖ የባሌውን ዥግና አዝማች እዳሉን ሲወጋ ሄደ (ተከለ ጻዲቅ መኩሪያ 1993፡ 432-434)።*

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው የአረብ ፈቂህ ገለጻ እንደተመለከተውና ተክለፃዲቅም (1993) እንዳብራሩት የሀዲያው እስላማዊው መንግሥት ሰይፍ እንዳይጠቀምና ኮርቻ የተጫነ ፈረስ ላይ እንዳይቀመጡ መከልከሉ በዘመኑ ለጦርነት ወሳኝ በሆኑ መሣሪያዎች ላይ በሀዲያው ሱልጣኔት ላይ በክርስቲያኑ መንግሥት የተጣለ ማእቀብ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የጦር መሳሪያ ማእቀቡ መነሻ ሲሆን የሚችለው ቀድሞ በነበሩት ዘመናት የሀዲያ ህዝብ ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር የነበረው ዘላቂ አለመግባባት ነው።

የጦር መሣሪያ ማዕቀቡ ያስፈለገበትን ምክንያት ተክለጻዲቅ (1993) ሲያብራሩ የሚከተለውን ብለዋል።

> *የሀዲያ ገራድ ወዲህ ለማቹ ወዲህ ለገዥው ንጉሠ ነገሥት በመታመን ፊንታ በፊት ይፋት በኋላ ሐረር የተቀመጠው የአዳል ሱልጣን በሸፈተ ቁጥር ወደዚያ እየተደረበ መሸፈት ስላስለመደ በሀገሩ ላይ ሰይፋ ጨብጦ ኮርቻ በፈረስ ጭኖ ሊዋጋ የሚችል ወታደር እንዳይመለምል በማለት መንግሥቱ (የክርስቲያኑ) ይህንን እርምጃ ወስዶ ይሆናል* (433) ።

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ፀሐፊ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ገራዶች በየዓመቱ ስለሚከፍሉት የሴት ልጅ ግብር ሲያብራሩ መታጠቧና መገነዟ ንፅህናዋን፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ያላቸውን ክብርና የሴቷን ልጅ እድለኛነት ሲያመለክት እንደሚችል ከተፈጠረው የሃይል ሚዛን መዛባት ጋር እያይዘው





በምሳሌ ቢያስረዱም እጅግ በጣም በተለመደው በሀዲያ ባህልም ሆነ በሌሎችም የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህል አጥቦ መገነዝና በቃሬዛ መጫን ለመጨረሻው ስንብት መዘጋጀትን የሚያመለክት ክንዋኔ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሀዲያው እስላማዊ ሱልጣኔት ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት ምን ያክል እንደማይፈልገውና በግዴታና በአቅም ልዩነት ምክንያት ብቻ እንደተቀበለውም ያመለክታል። በመሆኑም የሀዲያው እስላማዊ ሱልጣኔት ሳይመቸው ሲቀር ቢገብርም ዝምድናውና ግንኙነቱ በፍጹም ጥላቻ የተሞላ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

እላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በተጨማሪ የግራኝ ሀይሎች በሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ዙሪያ ያሉትን ህዝቦችና መንግሥታት ለምሳሌ የዳዋሮን፣ የፈጠጋርን፣ የገንዝን፣ የወጅን፣ የጉራጌን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ በኋላ የሀዲያ ሱልጣኔት ወደ ግራኝ ሀይሎች ጐራ መቀላቀሉ በሁለቱ እስላማዊ ሀይሎች መካከል በቆየው ወዳጅነትና ምናልባትም ድርድር ምክንያት ጠንካራ መተማመን መኖሩን ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪ አብሮ መሥራት የሚጀምሩበትን ትክክለኛ ወቅት እየጠበቁ እንዳነበረና የክርስቲያኑ መንግሥት ዳግም ትልቅ ስጋት መሆን በማይችል ሁኔታ ውስጥ ሲገባ የሀዲያ ሱልጣኔት ከግራኝ አህመድ ሃይሎች ጋር ተቀላቅሎ (ሃይሉን ደርቦ) መሥራት እንደጀመረ መገንዘብ እንደሚቻል የተለያዩ ጸሐፊዎች ያስረዳሉ (ተክለ ፃዲቅ፣1993)።

የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት የግራኝ አህመድን ሀይሎች በተቀላቀሉበት ወቅት ፖለቲካዊ ግንኙነቱን ሊያጠነክሩ የሚችሉ የጋብቻ ዝምድናዎች ከመፈጸማቸውም በላይ በተመሳሳይ ወቅት ሀይላቸውን በማስተባበር ወደ ባሌ አብረው እንደዘመቱ አረብ ፈቂህ ጠቅሷል። ይሄው ተመሳሳይ የአረብ

ጸሀፊ እንዳስረዳው በዚህ የባሌው ጦርነት በግራኝ አህመድ ጀኔራሎች የሚመራው ሠራዊት የባሌውን አዝማች አዳሉን በማሸነፋቸው አዝማች አዳሉም በጦርነቱ በመገደሉ አብሮ ከድል አድራጊዎቹ እስላሞች ወገን የተሰለፈው የሀዲያው ገዥ ከምርኮው፣ ከፈረሶቹም፣ ከሹማምንት ሚስቶችም፣ ድርሻውን ተካፍሎ ወደ ግዛቱ እንዲመለስ ከግራኝ አህመድ ፈቃድ አግኝቷል። ወደ ግዛቱ ከተመለሰ በኂላ በግዛቱ አካባቢ ያሉትን የክርስቲያኑ መንግሥት ደጋፊ ህዝቦችንና አካባቢያቸውን ለማቆጣጠር በሚደረገው የእስላሞች እንቅስቃሴ ሀዲያ አይነተኛ ድጋፍ አድርጓል። በአጠቃላይ ከ1531-1543 ያለው ጊዜ ሀዲያ ከክርስቲያኑ የአፄው መንግስት ተጽእኖ ፈፅሞ ነጻ ሆኖ የኖረበት ወቅት ነበር።

## 2.4.4. የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ በሀዲያ ህዝብ ላይ ያስከተላቸዉ አዳዲስ ሁኔታዎች

በ1543 ዓ.ም. የእስላም ሃይሎች በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ የነበራቸው የበላይነት ግራኝ አህመድ በወይና ደጋ ከመሞቱ ጋር ተያይዞ የሀይል ሚዛኑ ወደ ክርስቲያኑ መንግሥት እጅ ሲገባ የክርስቲያኑ መንግሥት የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ በጦርነቱ ወቅት ከእጅ የወጡትን የቀድሞ ግዛቶቻቸውን ማስመለስ ነበረ። በዚህ መሠረት ከልብነ ድንግል ቀጥሎ የነገሰው አፄ ገላውዲዎስ (1540-1559) በጦርነቱ ወቅት ከእጃቸው የወጡትን ግዛቶችን ለማስመለስ ያደረገው ዘመቻ አካል የነበረው እንቅስቃሴ በ1544 ዓ.ም. ሀዲያን እንደገና በክርስቲያኑ መንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውል አድርጓል።





ነገር ግን በ1544 የክርስቲያኑ መንግሥት በሀዲያ ላይ የተቀዳጀው የበላይነት ብዙም ሳይቆይ በአሚር ኑር ቢሙጃሀድ በሚመራውና ከግራኝ አህመድ ሞት በኂላ የተበታተነውን የእስላም ሃይሎችን ባሰባሰበው ጠንካራ ሀይል በዳዋሮ ጦርነት ንጉሥ ገላውዴዎስ በመገደሉ ከክርስቲያኑ መንግሥት ቁጥጥር ነጻ ሊወጣ ችሏል። ስዚህ በአሚር ኑር ስሚመረው አዲሱ ጅሃድ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱት ህዝቦች ዋናዉ የሀዲያ ህዝብ ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የሀዲያ ህዝብ የተሳተፈባቸው ረጅም የጦርነት ዘመናት የሀዲያን ህዝብ ጠንካራ ሀይል የጦርነቱን አቅጣጫና የሀዲያን ህዝብ የአሰላለፍ አስፈላጊነት ተከትሎ ወደ ዛሬው የደቡብ ክልል መኖሪያው በከፍተኛ ቁጥር እየተጠጋ እንዲመጣ ምክንያት እየሆነ ሄዷል። ለረጅም ጊዜ የቆየው በአሚር ኑር የሚመሪው የጅሃድ ጦርነት በመሪው በአሚር ኑር ሞት እስከበቃበት እስከ 1568 ዓ.ም. ድረስ ባሰው ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው የሙስሊም ህዝቦች አንዱ፣ የሀዲያ ህዝብ ነበረ።

በጦርነቱ ሰበብ፣ ለምሳሌ አብዛኞቹ የሀዲያ ህዝቦች ከከምባታ፣ጉራጌና ዋግ በስተምዕራብ ወደሚገኙ አካባቢዎች በበለጠ ቁጥር መንቀሳቀስ ግድ ሆኖባቸዋል። ይህ የሀዲያ ጠንካራ ሃይልና በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ከነበረበት ቦታ ወደ አዲስ አካባቢ መንቀሳቀስ በስምጥ ሸለቆ ምስራቃዊ አካባቢዎች ማለትም ቀድሞ የሀዲያ አገርና ጠንካራ ይዞታው በሆነበት ቦታ ላይ አንጻራዊ የሀይል ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። ይህ አዲስ ክስተት የሀዲያ አጐራባች ሆኖ ይኖር ስነበረውና የላይኛውን የገናሌን ወንዝ ደቡባዊ አቅጣጫ ይዞ ይኖር ስነበረው የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ችሏል።

የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ መሰረታዊ ምክንያቶች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሁኔታዎች መሆናቸው በተለያዩ ጸሀፊዎች ሲገለጽ፤ ህዝቡ ተንቀሳቅሶ ከተቆጣጠራቸው የመጀመሪያዎቹ አካባቢዎች የሚጠቀሰው ደሎ ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ የነበረው የሀዲያ ህዝብ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ቢቀላቀልም በአካባቢው ጕሳዎች እስከ አሁንም ሀዲያ ከፍተኛውን ቁጥር ይዞ እንደቀጠለ ይነገራል። በባሌ አካበቢም የነበረው የሀዲያ ህዝብ ከ1537 ዓ.ም. ጀምሮ በኦሮሞ እንቅስቃሴ የተዋጠ ሲሆን ብራውካምፔር (1980፡ 431) እንደተጠቀሰው በአካበቢው ያለው ማህበረሰብ እራሱን በሁለት ክፍሎ እንደሚመለከትና ነባር ኦሮሞና የሞጋሳ ኦሮሞ ተብለው እንደሚመደቡ ገልፆ፣ የሞጋሳ ኦሮሞ ሲባል ሀዲያን ያመለክታል ብሏል።

ብረውካምፔር (1980፡431) እንዳመለከተው በአጠቃላይ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በጣም የተጠናከረው የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ በረጅሙ በእስላሞችና በክርስቲያን መንግሥት መካከል በተደረጉ ጦርነቶች ለተዳከመው የሀዲያ ህዝብ ከለጣቸዉ ውስን አማራጮች ዋናዎቹ ለኦሮሞ ህዝብ እጅ በመስጠት መቀላቀል ወይንም አካባቢው በመልቀቅ ወደ ሌሎች ቦታዎች መንቀሳቀስ ነበሩ። ይህ ብራውካምፔር ለሀዲያ ህዝብ በዘመኑ የቀረበለት አማራጭ ነው ብሎ የጠቃቀሳቸዉ ምርጫዎች፣ የሀዲያ ህዝብ በወቅቱ ከነበነረበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የፈለገውን የመምረጥን ዕድል ጭምር አብረው የያዙ አልነበሩም። ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱም አማራጮች የሀዲያ ህዝብ መሠረታዊ ማንነትና ጥቅም የሚጻረሩ ናቸው።

የሀዲያ ህዝብ በዚህ ጠንካራ የኦሮሞ እንቅስቃሴ ጫና ውስጥ በነበረበት ወቅት የኦሮሞን ህዝብ እንቅስቃሴ መቋቋም ያልቻለው አፄ ሠርፀድንግል (1563-97) የሀዲያን ህዝብ እንደገና ወደ ክርስቲያኑ መንግሥት ቁጥር ለመመለስ ዘመቻ አካሄዷል።





የአፄ ሠርፀድንግል ዜና መዋዕል እንደሚያስረዳው አፄ የተባለው የሀዲያ ገራድ አልገብርም በማለት በ1568 ዓ.ም. በንጉሱ ላይ ሸፈተ። በ1569 ዓ.ም. ንጉሥ ሠርፀ ድንግል ሠራዊቱን ዋጀ ላይ (በደቡብ ሸዋ) ሰበሰበ። የሀዲያው ገራድ አልገብርም ብሎ እምቢ ሲል ከክርስቲያኑ መንግሥት የሚሰነዘርበትን ጥቃት እንደሚመክት በመተማመን ነበረ። ምክንያቱም በወቅቱ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት መሪ የነበረው ገራድ አዜ 1700 ፈረሰኛ ጦር ሲኖረው ከእነዚህም ውስጥ 500 ፈረሶች ከተባበሩት የእስላም ሃይሎች ጦር የተመለመለ ነበረ።

ይህ የተባበሩት የእስላሞች ጦር ተመልማይ ሰባል ጥሩር (cuiasses) የለበሱ ናቸው። ዜና መዋዕሉ እንደሚነገረው አፄ ሠርፀድንግል ያለ ጥርጥር ወደ ጦርነቱ እንደገባና የሀዲያን ጥሩር የለበሱ ፈረሰኞችን በማሸነፍ ወደ 300 የሚጠጉ ፈረሰኞችን ማርከዋል። ከዚህ ከመጀመሪያው ጦርነት የተረፈው የሀዲያ ሠራዊት እራሱን እንደገና በማደራጀት መልሶ መላልሶ የአፄ ሠርፀ ድንግልን ሠራዊት እንደተዋጋ በዜና መዋዕሉ ተጠቅሷል። በመጨረሻም አፄ ሠርፀድንግል ሀዲያን ማሸነፍ መቻላቸውንና መሪዎቻቸውም እጅ መስጠታቸውን በማስከተል በ1570 ከፋሲካ በኂላ የሀዲያን አካባቢ ለቀው ወደ ሰሜን አቅጣጫ ተንቀሳቅሰዋል።

ነገር ግን ከጥቂት ዓመታት በኂላ፣ የሀዲያ ህዝብ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ እንደገና አምጿል። በዚህ ምክንያት የአፄ ሠርፀድንግል ሠራዊት እንደገና ወደ ሀዲያ በመዝመት በጦርነቱ የሀዲያ መሪ የነበረውን ጀፈርን በመግደል በርካታ ከብት በምርኮ ዘርፏል። በ1577 ንጉሥ ሠርፀ ድንግል የተሸነፈውንና የተዘረፈውን የሀዲያን አገር በመልቀቅ ወደ ሰሜን ተመልሰዋል።

ከላይ እንደተመለከተው፤የአፄ ሥርፀድንግል ዘመን፣ በሀዲያና በክርስቲያኑ መንግስት መካከል ሌላው ክባድ ጦርነቶች የተካሄዱበት ወቅት ነበር። ምናልባትም በአፄው ዜና መዋዕል ንጉሱ ያስጥርጥር ከሀዲያ ጋር ሲዋጉ ወደ ጦርነቱ ገቡ የሚሰው አባባል በወቅቱ የነበረው የሀዲያ ሀይል እጅግ ጠንካራና ድፍረትን የሚፈትን እንደነበረ ሊያመለክት ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አፄ ሥርፀድንግል ካሉት ሌሎች ማዕረጐች በተጨማሪ የሀዲያ ገራድ የሚባለውን ማዕረግ ለራሱ መውሰዱ ምን ያክል ሀዲያን መቆጣጠር የንጉሱ መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን ሊያሳይ ይችላል። ይሀ ተመሳሳይ ወቅት የሀዲያ ጠንካራ ሀይል በደቡብ ምስራቅ አካባቢው በተለይም በባሌ፣ በሀረርና በደሎ የኦሮሞ ህዝብ እጅግ ጠንካራ የነበረው ህዝባዊ እንቅስቃሴ በአካባቢ የሀዲያ ህዝብ ላይ ያስከትል የነበረውን ከፍተኛ የሆነ የማንነት ማጣት ፈተና ለመቋቋም እንዳይችል ይልቁንም ዘመናትን ለተሻገረው ከክርስቲያኑ መንግሥት በኩል ለተጋረጠበት ፈተና ቅድሚያ በመስጠት ዋነኛ ጠላቱን ሲታገል የነበረበት ወቅት ነበረ።

አፄ ሥርፀድንግል በ1597 ዓ.ም. ድንገት ሲሞት ልጁ ያዕቆብ ዙፋኑን ወረሰ። በአፄ ያዕቆብ ዘመንም የሀዲያ አመጽ ስላልቆመ 1604 ዓ.ም. ንጉሱ በሀዲያ ላይ ዘመቻ ጀመረ። ነገር ግን ተስፋዬ (1993) ላጵሶ (2004) በመጥቀስ እንደጻፈው በክርስቲያኑ መንግሥት ልኡላን መካከል የነበረው የዙፋን ባላንጣነት እና የኦሮሞ ህዝብ ዘመቻዎች ተዳምረው የሀዲያ ህዝብ ከአፄ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ተጨማሪ ሁኔታዎችን ፈጥረዋል።

በክርስቲያኑ መንግሥት ውስጥ የነበረው የዙፋን እሽቅድድም 1607 ዓ.ም. በአፄ ሱስንዮስ የበላይነት ተጠናቆ አፄ ሱስንዩስ ከ1607-1632 የክርስቲያኑ መንግሥት ለመምራት በቅተዋል። በአፄ ሱስንዮስ ዘመንም የሀዲያ ህዝብ በገራድ ሲዲ መሪነት ለክርስቲያኑ መንግሥት አንገብርም ብሎ አመፁን ቀጥሏል።





አጥመጊዮርጊስ ወይም አስቃ አጥሜ የተባሉት የ20ኛው ክፍል ዘመን ፀሐፊ የዘመኑን የንጉሱን ዜና መዋዕል ጸሀፊዎችን መረጃ በመጠቀም የጦርነቱን ሁኔታ እንደሚከተሰው እንደጸፉት ተስፋዬ ጠቅሷል።

> *... ክረምቱ ካለፈ በኋላ በመስከረም አቤቶሁን ሱስንዮስ ከንጓታ ተነሣ ወደ ሀዲያ ሊዘምት ከሲዲ መሐመድ ጋር ሊዋጋ። ሲጓዙም ጉደር ወንዝ ደረሱ። ሠራዊቱም በዋና ተሻገረ። ከዚያም እንደ ገበጣን ሠፈረ ከአዋሽ መፍለቂያ። ከዚያ አንድ እጀም (መሪ) ገባለት ቀሶ የሚባል ሀያ ፈረሶኞች ጥቂት እግረኞችም ሆነው ከዚያም ወደ ውሪብ አለፈ፣ ከዚያ ጥቂት ጉራጌዎች ተቀበሉት። ከዚያም ሐዞ ሠፈረ፣ ሐዞ በሰፈረ ጊዜ መላ ጉረአጌ አርባ አረት ነገድ በክብር፣ በደስታ በእልልታ ተቀበሉት፤እንደ ነገሥታት ትክክል ክብር ለጡት፣ የአርበኝነት ሥራቸውንም በለልፍ አሳዩት። ከዚያም ሲዲን ለመውጋት መከሩት። እርሱም አፈጠነ፣ ከነጓዙ ከነገንዘቡ፤ ካለው ነገር ሁሉ ጋር ተጉዞ መንጋውንም ሳይተው ስንቁ ነውና። ሲዲ ግን ሠራዊቱ ሥፍር ቁጥር የሌለው ነበረ። ዳሩ ግን ከንጉሡ ልጅ ከሱስንዩስ ጋር መዋጋት ባይፈቅደው ወደ ዋቢ ወንዝ ሄደ። ሱስንዩስም ተከተለው። በዋቢ ወንዝም ደረሰበት። ከዚያም ጦርነት ሆነ፣ ጉራጌ በአንድ ፊት ኦሮሞ ባንድ ፊት ተሰለፉ። ባለቤቱ ከአማራ ጋር መካከል ገባ። ምድር እስክትቀረና ተዋጉ። ሲዲ ድል አደረገ። መጀመሪያ ጉራዓጌ ሸሸ። ቀጥሎም ኦሮሞ ሸሸ። ባለቤቱ ሲጋደል ከፈረስ ወጥቶ ሲመላለስ ፈረሱም ወደርሱ ሲወድቅ ክንድን ተመታ። ከሠራዊቱ ምንም አልተረፈም አለቀ። ከገንዘቡም መርፌ አልቀረውም። ከሲዲ እጅ ያመለጠ የለም። የማረከውንም ሰው ወደ ሐረር ለመሸጥ ሰደዳ። አቤቱሁን ሱስንዮስ ከሲዲ እጅ በጭንቅ አምልጦ ወደ ምድረ ይቢሾ ሄደ። ከዚያ ተነስቶ ወደ እነሞር አለፈ። ከእነሞር ወደ ሙገር። ከሙገር ሳለ ለብዕ እነሞር ከዲት፣ ከሲዲ ጋር ተዶለቱበት ጉራዓጌን ሰለፉ ከሲዲ ጋር ታረቁ። እነዚህ ከዳተኞች ክርስቲያኑን ጌታቸውን ለእስላም እሳልፈው*

> *ስለሰጡት ሲዲን እየመሩ እመጡበት። ሲዲም ሙገር በደረሰ ጊዜ ፅኑ የሆነ ውጊያ ተዋጉ። ከጧት እስከ ማታ ሰባት ቀን ሙሉ በሰባተኛውም ቀን ድል ባለመሆኑ ድል ባለማድረጉ እያቶ ከመኳንንቶቹ ጋር እንግዲህ ምን እናድርግ ወዴትስ እንሂድ? ብሎ መከረ። ... ምክሩን በተቀበለ ጊዜ ወደ ይቢሾ ተጓዘ እያዘነ እየተከዘ ስለገኘው መከራ። በተረት ካንተ ጋር መብላት ከሀዲያ ጋር መዋጋት እንዲሉ (ተስፋዬ፣ 1993: 40 - 41) ።*

ከላይ በተመለከተው በገራድ ሲዲና በአጼ ሱስንዮስ መካከል በተደረገው ውጊያ የተጠቀሱትን የቦታ ስሞችን መሃመድ (2009) ከአሁኑ መጠሪያቸው ጋር በንፅፅር መልክ አመልክቷል። በዚህም መሠረት ሐዞ ተብሎ ይጠራ የነበረው ቦታ በጉራጌ ውስጥ ገደባኖን ከስሜን ምዕራብ አቅጣጫ አቋርጦ የሚፈስ የግቤ ገባር ወንዝ የሚያካልለውን ሥፍራ ሲሆን ይቢሾ የሚለው ቃል የሙሁር ሌላው መጠሪያ ነው። ውርብ ምናልባትም የዛሬውን የወራቤ አካባቢ ሊያመለክት ይችላል።

በገራድ ሲዲና በአጼ ሱስንዮስ መካከል በተደገው ጦርነት መጀመሪያ ላይ የክርስቲያኑ መንግስት ለሀዲያ የአካባቢው ባለንጣዎች ከሆኑት ሀይሎች ጋር በመተባበር በጣም ከፍተኛ ግንባር መፍጠሩን እንመለከታለን። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ወቅት ማለትም በ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ የሀዲያ አገር ከጉራጌ እስከ ዋቢ ወንዝ ድረስ የሚዘልቅ ሰፊ ቦታን የሸፈነ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፤ ምናልባትም በዚህ በገራድ ሲዲና በሱስንዮስ መካከል በተደረገው ጦርነት ንጉሱ ከሲዲ እጅ በጭንቅ ማምለጡንና ከፈረሱም ወድቆ ክንዱን መመታቱን በመመልከት በገራድ ሲዲ የሚመሩት የሀዲያ ሀይሎች ቢያንስ ቢያንስ የንጉሱን ፈረስ መተው መጣላቸውንና ንጉሱንም ለመያዝ መቃረባቸውን መገንዘብ ይቻላል።





ከዚህም በተጨማሪ የሀዲያ ሀይሎች ለአካባቢያቸው ባላንጣዎች ምን ያክል አስፈሪዎች እንደነበሩ ለመረዳት የጉራጌ የተለያዩ ክፍሎች የነበራቸውን የወገንተኝነት መቀያየር ማየት ይቻላል። የመጨረሻውም የአጼ ሱስንዮስና የገረድ ሲዲ ጦርነት በሙገር አጠገብ ማለትም የክርስቲያኑ መንግስት ሰራዊት ወደ ሲዲ ሲዘምት መጀመሪያ በተሻገረው ወንዝ መካሄዱ የሲዲ ሀይሎች ረጅም ርቀት ከሀዲያ አገር ርቀው ሄደው በመዋጋታቸው ምክንያት አጼ ሱስንዮስን ዳግም ማሸነፍና መማረክ እንዳላስቻላቸው መረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ከ14ኛው እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ባሉት ጊዜያት የራሱን ማንነት ለማቆየት ከሦስት የተለያዩ ሀይሎች ጋር የተለያዩ ቅርፅ ያላቸውን ትግሎች አካሂዷል። ከሰሜኑ የክርስቲያኑ መንግሥት ጋር የነዘረው ትግል በጣም ረጅምና የማያቋርጥ የነበረ ሲሆን፣ ሁለቱም ሀይሎች የተለያዩ ዘዴዎችን በትግሉ ውስጥ ተጠቅመዋል። ጦርነትና የጋብቻ ዝምድና ግን በጣም የተለመዱ ዘዴዎች ናቸው።

በተለይም ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የጋብቻ ዝምድናን በትግሉ ውስጥ እንደ አንድ ዘዴ መጠቀምን በመተው ጦርነትን ብቻ ማተኮር እንደተመረጠ መገንዘብ ይቻላል። ምክንያቱም ለረጅም ዘመናት የተደረጉት የጋብቻ ዝምድናዎች እንደ አንድ ፖለቲካዊ ዘዴ በሀዲያና በክርስቲያኑ መንግሥት መካከል ሲፈለግ የነበረውን የክርስቲያኑን መንግስት የበላይነትና የሀዲያን ገባርነት ሊያረጋግጡ አልቻሉም።

## 2.5. የሀዲያ ህዝብ አጠቃላይ ሁኔታ ከ17ኛ እስከ 19ኛዉ ክፍለ ዘመን

በ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት የክርስቲያኑን መንግሥት ጦርነቶች መክቶ በመመለስ ነፃነቱን ማስጠበቅ የቻለበት ጊዜ ቢሆንም ወቅቱ የሀዲያ እስላማዊ ሱልጣኔት ከግራኝ አህመድ በኋላም ከኑር ሙጀሂድ የጂሃድ ሃይሎች ጋር በመተባበር የክርስቲያኑን መንግሥት ሲዋጋ በመቆየቱና በኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ምክንያት ጠንካራ ጫና እየገጠመው የመጣበት በመሆኑ የሀዲያ ህዝብ በቀድሞዎቹ የደቡብ ምሥራቅ ጥንታዊ መኖሪያዎቹ ማንነቱን ማጣት ቀጠለ፡፡ ስለዚህ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ ከሌሎች የእስልምና ሀይሎች ጋር በመተባበር የክርስቲያኑን መንግሥት መታገሉና ከኦሮሞ ተስፋፊ ሃይሎች ጋር የደረጋቸው ትግሎች ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር ለብቻዉ ካደረጋቸዉ ትግሎች ውጭ ያደረጋቸውን ትግሎችን ያመለክታሉ፡፡

የሀዲያ ህዝብ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ያደረገውን ትግል በተመለከተ እለቃ አጥሜን በመጥቀስ ተስፋዬ የሚከተለዉን ፅፏል፡፡

> *አፄ ሱስንዮስ በነገሠ በ16ኛው ዓመት በ1623 ዓ.ም በኦሮሞዎችና በሀዲያዎች መካከል ስለነበረው ሁኔታ የንጉሡ ወንድም ስዕለ ክርስቶስ እንዳተተው ሀዲያዎች ከኦሮሞዎች ጋር በመዋጋት ኦሮሞዎችን ለማሸነፍና ለመዝረፍ መቻላቸው አመልክተዋል (ተስፋዬ፡ 1993፡ 41-42) ፡፡*





ስለዚህ የሀዲያን ማንነት ከጠንካራዉ የኦሮሞ ተስፋፊ ሀይሎች ከመዋጥ ለማዳን ጠንካራ ትግል ሲካሄድ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም በመነሳት በ17ኛው ክፍለ ዘመን ለሀዲያ መንግሥት ከፍተኛ ፈተና የነበረው የክርስቲያኑ መንግስት ሳይሆን የኦሮሞዎች ግዙፍ እንቅስቃሴዎችና ጦርነቶች ነበሩ፡፡ ጉዳዩን ለሀዲያ መንግስት እጅግ አስከፊ ያደረገው የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ አቅጣጫ የሀዲያ ህዝብ ከስሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተለያዩ ምክንያቶች አፈግፍገው እስላማዊ ሱልጣኔታቸውን መስርተው በሚኖሩበት በዛሬው ሀረር፣ አሩሲና ባሌ ያነጣጠረ መሆኑ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሀዲያ ወታደራዊ ሀይል ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር ያደርግ የነበረዉን የውጊያና የትግል ግንባርና አቅጣጫን ተከትሎ ወደ ዛሬዉ የሀዲያ ህዝብ መኖሪያ ወደሆነው ደቡብ ኢትዮጵያ የተንቀሳቀሰበት ወቅት መሆኑ ለኦሮሞ ጠንካራ ተስፋፊዎች የሞጋሳ ሥርዓት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ይህ ጠንካራ የኦሮሞ ህዝባዊ እንቅስቃሴ የሀዲያን ህዝብ አብዛኛውን በቀድሞ መኖሪያቸው በኦሮሞዎች የሞጋሳ ሥርዓት ተውጠው እንዲቀሩ አድርጓል፡፡

ይህ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ያለው ዘመን ስለ ሀዲያ ህዝብ ታሪክና አኗኗር በአፈ ታሪክ መረጃዎች ብቻ በመመርኮዝ መረዳት የሚቻልበት ጊዜ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህ በአፈ ታሪክ ተመሥርቶ የሚሰጠው ዘገባና ትንተና የራሱ የሆኑ ድክመቶችና እጥረቶች ያሉት በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ቢኖርበትም ከ17ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ የሀዲያ ህዝብ ጊቾዎች /Giichchuwwa/ ወይም ጉሳዎች በተለያዩ አቅጣጫዎች ረጅም እመታትን በመንቀሳቀስ

ወደ ዛሬው የሀዲያ አገር እንዴት እንደደረሱ ብረውካምፔር የተባለው ጀርመናዊ ፀሐፊ አብራርቷል፡፡ ለምሳሌ የብራውካምፔር (1980) ሰፋ ያለ ዘገባ በጣም ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፣ የባዴኦሶ /Bade'ooso/ ሀዲያዎች ከደሎመና (ከባሌ) ተነስተው በ1870 ዓ.ም. ወደዛሬው መኖሪያቸው የደረሱት በገደብ፣ በሸዋ፣ በከተራ፣ በሐረዋ፣ በገሱባ፣ በዳሞት፣ እና በብሰቴ ሽለቆ በማለፍ ነበር፡፡ ከደሎ እስከ ሸዋ ድረስ የነበረው እንቅስቃሴ ግን የክርስቲያን መንግስት ጠላት ከሚሆኑት የአዳል ሃይሎች ጋር በጋራ ያደረጉት እንደነበረ ይገለፃል፡፡

የሌሞ /Leemo/ ጊቾ /Giichcho/ በአባያ ሀይቅ አካባቢ ከዋራ በመነሳት በአልበሶ (አርሲ) ፣ በማረቆና በእነሞር አድርገው ብዙ መቶ አመታትን በመንቀሳቀስ ወደ ዛሬው የሌሞ /Leemo/ አካባቢ የደረሱት ከ1760-1900 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ረጅም ጊዜያት ዉስጥ እንደነበረ ይገለፃል፡፡ የሻሾጎን /Shaashoogo/ ጊቾ /Giichcho/ በተመለከተም የማህበረሰቡ አፈ ታሪክ እንደሚያስረዳ ከሴሩ (ከሰሜን ምሥራቅ አዋሽ) አካባቢ በመነሳት በከተራ (አሩሲ)፣ በገደብ፣ በሻሽመኔ፣ በሻላ ሐይቅ፣ በባሶ፣ በከንባታና በስልጤ በማለፍ ከሁለት መቶ አመታት በኂላ ወደ ዛሬው መኖሪያቸው የደረሱት በ1770 ዓ.ም. ገደማ እንደነበረ ይነገራል፡፡

ከሀዲያ ጊቾ /Giichcho/ የሶሮ /Sooro/ ጊቾን/Giichcho/ እንቅስቃሴ በተመለከተ የማህበረሰቡ አፈ-ታሪክ እንደሚደስረዳው ከገደብ /ከላይኛው ዋቢ ሸበሌ/ አካባቢ በመነሳት በፈጠገር፣ በላንጋኖ ሐይቅና በዝዋይ ሸለቆ፣ በማረቆ /ሊብዶ/ በወይባና በጉራጌ አድርገው ከብዙ መቶ ዓመታት በኂላ ወደ ዛሬው የሶሮ አካባቢ የደረሱት ከ1760-1800 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ጊዜያት እንደነበረ ይገልፃል፡፡





ሌሎች የሀዲያ ጊቾዎች ወደዛሬው የሀዲያ አካባቢ ከመድረሳቸውም በፊት ጀምሮ በአካባቢው ህዝቦች ላይ የበላይነት የነበራቸው የሀዲያ ቡድኖች እንደነበሩ ይነገራል (ብራውካምፔርና ጥላሁን 1999፣ 20) ፡፡

የልብዶ /Libido/ ወይም ማረቆ /Maaraqo/ ሀዲያን በተመለከተም ያለው አፈ-ታሪክ እንደሚያስረዳው የቀድሞ መኖሪያቸው ከነበረው ከዝቋላ ተራራ አካባቢ በመፍለስ በዝዋይ ሐይቅና በላይኛው የብላቴ ወንዝ መካከል ያለውን ቦታ እንደተቆጣጠሩ ይነገራል፡፡ ይህንን ማረቆ ተብሎ የሚጠራውን አካባቢ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የልብዶ /Libido/ ሀዲያዎች ተቆጣጥረውት እንደነበረም መረዳት ይቻላል፡፡

የቀቤና /Qabeena/ ና የአለባ /Alaaba/ የሀዲያ ጊቾዎችን /Giichchuwwa/ በተመለከተም ማህበረሰቡ 1720 ዓ.ም. አካባቢ የቀድሞ መኖሪያው ከነበረው የሲዳማ አካባቢ ተንቀሳቅሶ የብላቴን ወንዝ በመሻገር በጠንባሮ አጠገብ እንደሰፈረ ይነገራል፡፡ ከዚህ የሰፈራ ቦታው 1790 ዓ.ም. አካበቢ ወደ ሰሜን እንቅስቃሴያቸው በመቀጠል ከጉራጌ ተራራዎች በስተደቡብ በሚገኙት ዋቸሞና ጉና በተባሉ አካበቢዎች ሰተወሰኑ ጊዜ መኖራቸዉ ይነገራል፡፡ ከዚህ ቦታ በ1815 ዓ.ም. አካባቢ በመቀንቀሳቀስ የቀቤና /Qabeena/ ሀዲያዎች ወደ ሰሜን እንቅስቃሴያቸውን በመቀጠል በእነሞርና፣ በቸሀ በማለፍ በ1860 ዓ.ም. አካባቢ ዜና ባነር የተባለውን አካባቢ በዘላቂነት እንደተቆጣጠሩት ይነገራል፡፡ የአላባ /Alaaba/ የሀዲያ ጊቾ /Giichcho/ ከዋቸሞና ጉና አካባቢዎች በምሥራቅ አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ሁልባረግ ላይ ለጥቂት አመታት እንደሰፈሩ ይነገራል፡፡ ከዚያም በ1825 ዓ.ም. ጀምሮ እንቅስቃሴያቸውን በመቀጠል ኡል አላባ ተብሎ ከሚታወቀው ሌላው የአለባ ቡድን ጋር ከብለቴ ወንዝ በስተምሥራቅ እንደሰፈሩ ይነገራል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት በሀዲያ ጊቾዎች ዝርያዎችና ሌሎችም በአብዛኛው በጣም ጠንካራ በነበረው የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ወቅት በተለያዩ የዛሬዎቹ የኦሮሞ አካባቢዎች ለምሳሌ በአርሲ፣ በባሌ፣ በሀረርና በሸዋ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ተዋህደው እንደቀሩ ይነገራል፡፡ ብረውካምፔር (1980፡ 428) ለምሳሌ፣ በአርሲ ውስጥ ብቻ የሚገኙት የሀዲያ ጐሳዎች ቁጥራቸው ወደ ሁለት ሚሊዮን /2,000,000/ እንደሚደርስ በመግለፅ ይህ የሀዲያ ጐሳዎች ቁጥር ከሌሎች ከተቀሩት የአሩሲ ኦሮሞ ጐሳዎች በእጅጉ እንደሚበልጥ ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ተውጠው የቀሩትን የሀዲያ ማህበረሰቦች ዝርያዎች ቁጥር ከ2 እስከ 3 ሚሊዮን እንደሚደርስ ብረውካምፔር (1980) ያስረዳል፡፡

ተስፋዬ (1993፣446-447) ብራዉካምፔር (1980፡427)ን በመጥቀስ እንዳስቀመጠዉ በኣሩሲ ኦሮሞዎች መካካል ብቻ የሀዲያ ዝሪያቸዉን የሚያስረዱ ከ100 በላይ የሀዲያ ጎሳዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም ዉስጥ የሚከተሉት በሚሳሌነት ተጠቅሰዋል፡፡

*አበና፣ አባይመና፣ አቦሳ፣ አቦሰራ፣ አብሮኄ፣ አቡሬ፣ አንጀዳ፣አሪያ፣አሰሳ፣አዳሞኜ፣አደሬ፣አዳርሾ፣ዳይመና፣ አጀ፣ኪያ፣አሲ፣አመንዱላ፣አሚኛ፣አንጀዳ፣አሪያ፣አሰላ ፣አሻመራ፣ አታቦ፣ አሎጃና፣ ወይም ሻምምአና / ሻመና/፣ አይመራ፣ ባደሳ፣ በሃሙዳ፣ በስመና፣ በርበሬ፣ ብዲቃ፣ ቾፍራ፣ ጫትመና፣ ዳይ፣ ደሊቤ፣ ዶዳ፣ ኤጎ፣ ፈራቾ፣ ፈረጃ፣ ፈረዛና፣ /ፈርሳና/፣ ፉናሙራ፣ ጋሰማ፣ ጋሰላ፣ ጀዋራ፣ ጀዊ፣ ጂዳ፣ ጅልንሻ፣ ጉፍንግራ፣ ጎማራ፣ ሃባራኖላ፣ ሀባሎላ፣ ሃንጌዳ፣ ሃሪመና፣ ሃዋጡ፣ ሄላ፣ ሄጦሳ፣ ሆልበትመና፣ ሁዱጋ፣ ሁንቴ፣ አሰኒ፣ አንሴመና፣*





*ካጀዋ፣ ቀላሳ /ከላሳ/፣ ቆንቻቆቻ፣ ቂጣ፣ ኮልምኔ፣ ቆማ፣ ቆራብዶ፣ ለታመና፣ ሊሙ፣ ሎዴ፣ ማደዳ፣ መዳርሾ፣ ሜሼራ፣ ንጉዬ፣ አዴመና፣ ራይቱ፣ ራይዋመና፣ ሰብሮ፣ ሲዴ፣ ሽፍላ፣ ሽከማራ፣ ሳላይመና /ሳሲመና/ ሻሾጎ፣ ሲዋዴ፣ ሳይመና፣ ሼደማ፣ ሼካ፣ ሰልጢአና፣ ሲናና፣ ስሬ፣ ሶሌ፣ ሶሮ፣ ሱዴ፣ ሹኔ፣ ተማና፣ ተዋጃ፣ ጤቾ፣ ሑብመኖላ /ሁበመኖላ/፣ ዋቸምመና /ዎቸመና/፣ ዋግድመና፣ ዌጌ፣ ዌራራ፣ ዎላሴ፣ ዋምባዬ፣ ዎናመና /ዎናምቹ/፣ ዋሽርምኔ፣ ዎንሸበራ / ዎይስጠራ/፣ ዎትስአና /ዎትስመና/ ያብሰና፣ ሄበኒ፣ እና ያኩማ፡፡*

ከነዚህ ክላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በሀረርጌ በኢቱ ባሬንቱ እከባቢዎች *አቦሰራ፣ አሰልመና፣ ዶዮመና፣ ሆራሱመና፣ ቶቃመና፣* በባሌ በዶሎመና አካባብ *ገበርቾ፣ ሴማና፣ ባዴመና፣ ሆልበትመና፣አባይመና፣*እና በወላይታ ዉስጥ *አንሶሜ፣ ቦሃልመና፣ ዳዌኤ፣ ሄሮገራ፣ ጀዋሮ፣ ሀበሉ፣ ኦሊችመና፣ ዎራልአሶ፣ ሳሮሶ፣ ማይአሶ፣ ሜሼራ፣ ሞጨ፣ ዋጌሽመና፣ አባመና፣ እጎመና፣ ሃንዴሮ፣አኒመና፣ ቡሬአሶ፣ኤፎ፣ ዳጌኤ* እና የመሳሰሉት የሀዲያ ጎሳዎች እንደሚገኙ ተስፋዬ (1993: 451) ሲገልጽ የሀዲያ ሽማግሌዎችም ተመሳሳይ አስተያየት አላቸዉ፡፡

ስለዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ብራውካምፔርና ጥላሁን (1999: 21) ሲያብራሩ ከአጠቃላይ የሀዲያ ህዝብ ውስጥ የራሳቸውን ማንነትና ቋንቋ አስጠብቀው ለቆዩት የሀዲያ ህዝቦች የሥምጥ ሸለቆ ዝቅተኛ ቦታዎችና በብላቴና ኦሞ ወንዞች መካከል የሚገኙ ተራራማ አካባቢዎች የመጨረሻ ይዞታቸው ሊሆኑ ችለዋል፡፡

የሀዲያ ህዝብን ከኦሮሞ በህልና ቋንቋ ጋር መዋሁ፡ን ቀድመው የኦሮሞን የበላይነት የተቀበሉ ሀዲዮች ራሳቸው እንዳገዙና የሀዲያ ህዝብ የመሃላ ወይም ሀድሮ ባህል ከኦሮሞ ህዝብ ባህል ጋር መመሳሰሉም ለመዋሃድ ከፍተኛ እገዛ

እንዳደረገ ይነገራል። በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሀዲያ ህዝብ ተውጦ በቀረበት በአሩሲ አካባቢ ማለትም ከዝዋይ ሀይቅ እስከ ዋቢ ሸበሌ እና ከላይኛው አዋሽ ወንዝ እስከ ገናሌ ባሉት ቦታዎች ምንም እንኳን የቋንቋና የባህል ተመሳሳይነት ቢንፀባረቅም በአንዳንድ መስኪያዎች ሁለት አይነት ማህበረሰቦች አብረው የሚኖሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንደሚቻል ብራውካምፔር (1980፡ 431) ይገልፃል። ለምሳሌ፣ በቁጥር አናሳ ከሆኑት የኦሮሞ ጐሳዎች የገዳ መሪዎች ሲመረጡ አብላጫ የሆኑት የሀዲያ ጐሳዎች በእስልምና ሃይማኖት ተከታይነታቸው ይታወቃሉ።

በዚህም መሠረት ከህዝቡ ከሁለት ሦስተኛ በላይ ከሚቆጠሩት የሀዲያ ጐሳዎች በስተቀር የተቀሩት የኦሮሞ ጐሳዎች የኦሮሞን ባህላዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ነበሩ። በመሆኑም የሀዲያ ጐሳ የሆኑ የአሩስ አካባቢ ኦሮሞዎች ከኦሮሞ ጐሳዎች ያነሳ ቦታ ይሰጣቸው እንደነበረ (ዚኒከማሁ: 431) ፅፏል። ነገር ግን የእስልምና ሃይማኖት በሁሉም የአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ተቀባይነቱ እየጨመረ መሄድን ተከትሎ በሀዲያ ኦሮሞዎችና በነባር ኦሮሞዎች መካከል የነበረውን ልዩነት በእጅጉ ቀንሷል።

የእስልምና ሃይማኖት በአሩስና በሌሎችም በደቡብ ምሥራቅ የቀድሞ የሀዲያ አካባቢዎች መስፋፋትና የኦሮሞን ባህላዊ ሃይማኖት እየተካ መሄድ እንዲሁም እንደባሌው ሼክ ሁሴን ያሉ ቦታዎች ለሙስሊሙ የደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ማህበረሰብ እንደ ቅዱስ ስፍራ መወሰድ በአሩሲ ውስጥ ያሉት የሀዲያ ጐሳዎች ባህላዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ ዕድል ሰጥተዋቸዋል።

ከላይ ከተገለጸው ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው ለሀዲያ ህዝብ መዳከምና በኋላም ላይ በዛሬው በጣም ውስን በሆነ ቦታ ብቻ መቅረት ምክንያት ነው ተብለው ከሚጠቀሱት ነገሮች መካከል





ለምሳሌ፣ ለረጅም ዘመናት የዘለቀውና ከተለያዩ ሀይሎች ጋር በህብረትም ሆነ በጠላትነት የተደረጉት ጦርነቶች፣ የኦሮሞን ህዝብ ጠንካራ የሆነ የመስፋፋት እንቅስቀሴ ተቀብለው የተቀላቀሉ የሀዲያ ቡድኖች ማንነታቸውን አስጠብቀው ለመቆየት ቁርጠኝነትና አቅም ማጣት ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው ተብሎ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከላይ የሀዲያን አፈ-ታሪክ መነሻ በማድረግ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በሀዲያ ህዝብ ታሪክ ላይ የተከሰቱትን መሠረታዊ ለውጦችን፣ ለውጦቹን ያስከተሉ ሁኔታዎችንና የለውጦቹን ውጤቶች ብራውካምፔር (1980)፣ ብረውካምፔርና ጥላሁን (1999) እና ተስፋዬ (1993) የፃፉትን ፅሑፎች መሠረት በማድረግ ስንመለከት የሚከተሉትን መሠረታዊ ሀሳቦች ማግኘት ይቻላል።

የህዝቡን ከደቡብ ምስራቅ ስፊው ይዞታውና እጅግ ጠንካራ ከሆኑት አጐራባች የሙስሊም ሱልጣኔቶች ተነጥሎ ወደ ዛሬው ደቡባዊ ዋነኛ የሀዲያ አካባቢ መንቀሰቀስን የፈጠረው በዘመኑ የነበሩት ጦርነቶች እንደነበሩ መረዳት ይቻላል። እንቅስቃሴዎቹም በመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር የተደረጉ የጦርነቶች እንቅስቃሴ አቅጣጫዎች በመከተል ተጨማሪ ቦታዎች ከመያዝ ውጪ የቀድሞ መኖሪያ አገርን በአጠቃላይ በመልቀቅ አዲስ ስፈራ ማካሄድን የሚያመለክቱ አይመስሉም።

የኦሮሞን ህዝብ ጠንካራ የመስፋፋት እንቅስቃሴንም ተከትሎ የተከሰተው ሁኔታ የሚጠቁመው በጣም ሰፊ በሆነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ላይ ሀይሉ ተበትኖ በሚገኘው የዘመኑ የሀዲያ ህዝብ ላይ የተጋረጠ በጠንካራ የኦሮሞ ህዝባዊ እንቅስቃሴ የመጥለቅለቅ ፈተና መሆኑን ነው። ይህንን ጠንካራ ፈተና ለመቋቋምና የሀዲያን ታሪካዊ ማንነት

ለማስጠበቅ የሀዲያ ሀይሎች ከኦሮሞዎች ጋር ጦርነት መግጠማቸውና ችግሩን ለመቋቋም ያደረጓቸው ጥረቶች ተገልጸዋል፡፡ ምንም እንኳን ጦርነቱ የት አካባቢ ላይ እንደተደረገ ማወቅ ባይቻልም በተጠቀሰው ዘመን (1623 ዓ.ም.) አካባቢ ጠንካራው የሀዲያ ወታደራዊ ሀይል በነበረበት አካባቢ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በኦሮሞ እንቅስቃሴ ወቅት የሀዲያን ሕዝብ የቀድሞ መኖሪያ አካባቢዎችን ለመቆጣጠርና ህዝቡን ወደ ኦሮሞነት ለመቀላቀል ከፍተት የሰጠውና ምቹ ሁኔታን የፈጠረው ከኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ በፊት የነበረው የታሪክ እውነታና በሀዲያና በኦሮሞ ህዝቦች መካከል ለዘመናት የዘለቀው የባህልና የሥነ ልቦና ተመሳሳይነት ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ለአብዛኛው የሀዲያ ጎሳዎች ቋንቋ እና ባህል በኦሮሞነት መተካትም ሆነ ዛሬ ድረስ በጥንካሬ ለቀጠለው የሀዲያ ማንነት፣ ቋንቋና ባህል መቀጠል ዋነኛ ምክንያት በክርስቲያኑ መንግሥትና በእስልምና የተባበሩ ሀይሎች መካከል ይደረጉ የነበሩ ጦርነቶች መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሀዲያ ህዝብ ከክርስቲያኑ የሰሜን ኢትዮጵያ የተለያዩ አፄዎች ጋር ያደርጋቸው ከነበሩት ጦርነቶች ጋር ተያይዘው የሚነሱትን የተለያዩ የአካባቢ ስሞችንና የእነዚህን አካባቢዎች ጂኦግራፊያዊ መገኛ እንዲሁም ከሀዲያ ህዝብ አንፃር መገኛው የሚሰጠውን ትርጉም በማጥናት የዛሬ የሀዲያ ህዝብ መኖሪያ የሆነው አካባቢ የተለያዩ የሀዲያ ጊቾዎች /Güchchuwwa/ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ የተናጥል የስደት ጉዞ ካደረጉ በኋላ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ብቻ በቋሚነት የተቆጣጠሩት ነው የሚለውን አስተሳሰብ መጠራጠር ይቻላል፡፡

ለምሳሌ በ1316/17 ንጉሥ አምደ ፅዮን በሀዲያ ህዝብ ላይ የዘመቱ ሲሆን የዘመቻ ጉዞ መንገድ የነበረው የክርስቲያኑ





መንግሥት ደቡባዊ ወረዳ በነበረው በአይመለል /ጉራጌ/ በኩል በማድረግ እንደነበረ ተገልጿል፡፡ ተክለ ፃዲቅ (1993፡ 432-434) አረብ ፈቂህን በመጥቀስ እንዴት የሀዲያ ሱልጣኔት የግራኝ አህመድ ሀይልን እንደተደረበ ሲገልጽ በሀዲያ አካባቢ የነበሩትን የክርስቲያን መንግሥት ደጋፊ ሕዝቦችና አካባቢዎችን ጠቅሷል፡፡ ከእነዚህም መካከል የከምባታ ህዝብ በዋናነት ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የ14ኛው ክፍለ ዘመን ታሪካዊ እውነታዎች የዛሬው የሀዲያ ህዝብ ጉረቤት የሆኑት የጉራጌና የከምባታ ህዝቦች ከተጠቀሱት ዘመናት ጀምሮ ከሀዲያ ህዝብ ጋር በጉርብትና ይኖሩ እንደነበረ በግልፅ ያስረዳሉ፡፡

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ማስረጃዎች በተጨማሪ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ውስጥ የሀዲያ ህዝብ በገራድ ሲዳ መሪነት ከአፄ ሱስንዮስ ጋር ያደረገውን ጦርነትና ድል በማጥናትና ንጉሥ ሱስንዮስ ወደ ሀዲያ አገር ለጦርነት የመጡበትን አቅጣጫ በመመልከት፣ በወቅቱ (17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ) የሀዲያ ጠንካራ ወታደራዊ ሀይል መገኛና ከኦሮሞ መስፋፋትም ሆነ ከክርስቲያኑ መንግሥት ቁጥጥር ነፃ የነበረው አገር፣ ከዋቢ ሸበሌ ወንዝ ደቡባዊ ጫፍ ከገደብ አካባቢ ተነስቶ በደቡብ ምዕራብ ትንሹ ዌብ ከግቤ ወንዝ እስከሚገናኙበት ያለው ቦታ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ገራድ ሲዳ ከንጉሥ ሱስንዮስ ጋር ብቻ ሳይሆን በንጉሡ ወዳጅነታቸውና ዝምድናቸው ጭምር ከሚታወቁት የዘመኑ የኦሮሞ ሀይሎችና ከጉራጌ ጋር የጋራ ግንባር ጦርነት እንዲቀር በመመኘት እስከ ዋቢ ወንዝ ድረስ ማፈግፈጉን እጥሜ ጊዮርጊስ የጻፉትን ስንመለከት በተጠቀሰው ዘመን በምሥራቅ አቅጣጫ እስከ ዋቢ ሸበሌ ደቡባዊ አካባቢ እስከ ገደብ ያለው ቦታ በኦሮሞዎች ቁጥጥር ሥር እንዳልነበረ

እንዳልነበረ እንረዳለን፡፡ አቤ ሱስንዮስና የንጉሱ ደጋፊዎች የነበሩት የኦሮሞና የጉራጌ ሃይሎች ጉራጌን ተሻግረው በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ገራድ ሲዲን ለመውጋት ወደ ሀዲያ አገር የገቡበትን የደቡብ ምዕራብ ጫፍ ተስፋዬ (1993) የሀዲያ ማህበረሰብ እ.ኤ.አ. በ1500 ዓ.ም. ገደማ የያዛቸውን ቦታዎች ለማመልከት በተጠቀመው ካርታ የዛሬዎቹ ሁሉም የሀዲያ ጊቾዎች በ15ኛው ክፍለ ዘመንም በዚሁ ተመሳሳይ ቦታዎች ይኖሩ እንደነበረ ሲያስረዳ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ወደ ግቤ ወንዝ የተጠጋ ድንበር እንደነበራቸው ካርታው ይጠቁማል፡፡

ከዚም በተጨማሪ አቤ ሱስንዮስ ከሀዲያ ዘመቻ ተሸንፎ ሲመለስ የተከተላቸውን የጉዞ አቅጣጫዎችና የቦታ ስሞች እንደተመለከተው ስንገመግም በዛሬው የጉራጌና የስልጤ ዞኖች የሚገኙትን የተለያዩ አካባቢዎችን ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም ዛሬ ቋንቋቸውን፣ ታሪካቸውንና ማንነታቸውን አስጠብቀው የሚኖሩ የሀዲያ ጊቾዎች የሰፈሩበት ቦታ ቢያንስ ቢያንስ ከ14ኛው ክፍለ ዘመንም ጀምሮ የሰፊው የሀዲያ አገር አካል እንደነበረ መረዳት ሲቻል፣ በዚህ አካባቢ የሀዲያን መሠረታዊ ማንነት አስጠብቆ ለማቆየት ዋነኛ ምክንያት ሊሆን የቻለው በዘመኑ የሀዲያ ጠንካራ ሀይል የተከማቸበት አካባቢ መሆኑ ይመስላል፡፡

በዚህ አስተሳሰብ መሠረት የሀዲያ የተለያዩ ጊቾዎች ከተለያዩ የሀዲያ ሱልጣኔት ጫፎች በኦሮሞዎች መስፋፋት ግፊት በተለያዩ አቅጣጫዎች ብዙ ዘመናትን የፈጀ ጉዞ በማድረግ ወደ ዛሬው የሀዲያ አካባቢ በተለያዩ ወቅቶች ደረሱ የሚለውን አፈ ታሪክ አምኖ ለመቀበል በቂ የሆነ ማስረጃ ያስፈልጋል፡፡

የሀዲያ ህዝብ የዛሬዉን የሀዲያ መኖሪያ አከባቢ ባለቤት የሆነዉ በ19ኛዉ ክፍለ ዘመን ነዉ የሚለዉ አስተሳሰብ አጠራጣሪነት ከሚያመለክቱት የካርታና የጽሁፍ ማስረጃዎች





በተጨማሪ እያንዳንዱ የሀዲያ ጊቾ (ሌሞ፣ ሶሮ፣ ሉሩስ፣ ዌጠጊራ፣ ቀቤና፣ አላባ፣ ማረቆ፣ ባዱአስ፣ ሻሾጉ እና ሌሎችም) በርካታ ዓመታትን በፈጀው የጉዞ ወቅት ከሌሎች ህዝቦች ጋር በነበራቸው መስተጋብር ወይንም ከሌሎች የሀዲያ ጊቾዎች በመነጠላቸው ምክንያት ያጧቸው መሰረታዊ የማንነት መገለጫዎች አለመኖራቸው ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ረጅም አመታትን የፈጀው የተናጥል ጉዞ በምንጮች የተጠቀሱትና ከሌሎች በጉዞ አቅጣጫ ከነበሩት ህዝቦች ጋር የነበሩት ግንኙነቶች ሊፈጥሩ ይችሉ የነበሩት የቋንቋ፣ የባህልና የሥነ-ልቦና ልዩነት በምን አይነት ምክንያት ሊከሰት እንዳልቻለ የሀዲያን ትውፊታዊ ማስረጃ በመጠቀም ዘመኑን የተነተኑ ጸሀፊዎች አላብራሩም፡፡

ለዚህ አሳቤ ማሳያ ሲሆን የሚችለው የአላባና የቀቤና ሀዲያ በአንድነት በግምት ከ1720-1790 ባለው የ70 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ከጠንባሮ[22] ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ጉን በመስፈራቸው የቀድሞ ቋንቋቸውን በመተው የተለየ ቋንቋ ተናጋሪ መሆናቸው ሲገለጽ፣ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ በተለያዩ አካባቢዎች በመስፈር ከተለያዩ ህዝቦች ጋር ግንኙነትና መስተጋብር እየፈጠሩ ተንቀሳቅሰው ወደ ዛሬው የሀዲያ ክልል ደረሱ የተባሉት ለምሳሌ የሶሮ /Sooro/ ፣ የሌሞ /Leemo/፣ ወይንም የሻሾጉ /Shaashoogo/ ሀዲያ ጊቾዎች /Giichchuwwa/ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በምን መልኩ ማስጠበቅ እንደቻሉ የሚገልጽ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም (ብራውካምፔር፣1980: 432)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዌጠ ጊራ ሀዲያዎች ከግራኝ አህመድ ጦርነት ዘመን ጀምሮ (16ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያው አጋማሽ) እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ

[22] የጠንባሮ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ከከንባታ ህዝብ ጋር በደቡብ ብሄር፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የጋራ ዞን መስርተዉ የሚኖሩ ናቸዉ፡፡

በከምባታ ህዝብ ላይ የበላይነት እንደነበራቸውና ከባድ ጭቆናም ያደረሱ እንደነበረ የተገለጸ ሲሆን (ብራውካምፔርና ጥላሁን፣ 1999: 20) በዚህ ሁሉ ዘመን ግን አንዳቸውም በዋነኛነት ማንነታቸውንና ቋንቋቸውን እንዳላጡ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይልቁንም ይህ ከላይ የተጠቀሰው የዌጠጊራ (weexxogiira) ሀዲያዎችና የከምባታ ህዝብ ግንኙነት ታሪክ ሀዲያ በተጠቀሰው ዘመን በዛሬው የሀዲያ አካባቢ ይኖር እንደነበረ ያስረዳል፡፡

የሀዲያን የተለያዩ ጊቾዎች (Giichchuwwa) የቀድሞ መኖሪያቸውን በመልቀቅ ረጅም ዘመናትን ተጉዘው ወደ ዛሬው የሀዲያ አገር ሲደርሱ በብራውካምፔር (1980)፣ ብራውካምፔርና ጥላሁን (1999)፣ ተስፋዬ (1993) አፈ-ታሪኩ እንደሚያስረዳ፣ በዛሬዎቹ የሀዲያ ወረዳዎች ተረጋግተው ከመስፈራቸው በፊት አንዱ ጊቾ ከሌላው ጋር መዋጋትና መገፋፋት የመጨረሻው ዕጣቸው ነበረ፡፡ ለምሳሌ ሶሮ ከሌሞ ጋር፣ ሻሾጉ ከዌጦ ጊራ ጋር፣ ሌሞ ከቀቤናና አላባ ጋር ግጭት ዉስጥ ገብተዉ እንደነበረ ተገልፆል፡፡ ከጉረቤት ህዝቦችም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሰላማዊ እንዳልነበረ በሁሉም አቅጣጫዎች ግጭቶችና መገፋፋቶች እንደነበሩ አፈ-ታሪክን መነሻ በማድረግ ከላይ የተጠቀሱት ጸሃፊዎች የጻፉት የምርምር ሥራዎች ያመለክታሉ፡፡ በተመሳሳይ ጸሃፊዎች እንደተገመተው (ትውልድን በመቁጠር) ይህ በሀዲያ ጊቾዎች መካከልና የሀዲያ ጊቾዎች ከዛሬዎቹ አጉራባች ህዝቦች ጋር የነበራቸው ግጭቶችና ጦርነቶች የተከሰቱት በዋነኝነት ከ18ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ሩብ ጀምሮ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ባለው ጊዜ ነው፡፡ የግጭቶቹንና የጦርነቶቹን መሰረታዊ ምክንያቶች ከፅሑፎቹ መረዳት እንደሚቻለው የዛሬውን የመኖሪያ መሬታቸውን በባለቤትነት ለመያዝ የሚያደርጉት ትግል ውጤቶች እንደነበሩ መገንዘብ አያስቸግርም፡፡





ስለዚህ ብራውካምፔር (1980)፣ ብራዉካምፔሪና ጥላሁን (1999)፣ ተስፋዬ (1993) አፈታሪክን መነሻ በማድረግ ባለፈሩት ጽሁፍ መሰረት የዛሬዎቹ የሀዲያ ጊቾዎች አሁን የያዙት መሬት ባለቤት የሆኑበት ዘመን ሌሎች የጽሁፍ ማስረጃዎች የሀዲያ ህዝብ የአካባቢው ባለቤቶች ነበሩ ብለው ከሚጠቁሙት ዘመን እጅግ ወደ ዛሬ የቀረበ /recent/ ነው፡፡ ይህ ሌላው ጽሁፉን አጠራጣሪ የሚያደርግ ነጥብ ነው፡፡ በተለይም ዛሬ በሀዲያ ጊቾዎች መካከል ያለውን የቋንቋ፣ የስነ ልቦና፣ የባህል፣ የግንኙነትና የመኖሪያ ቦታ ተመሳሳይነት በመመልከት ሀዲያ ዛሬ የያዘውን መሬት አንዱ ጊቾ /Giichcho/ ከሌላው ጋር እየተዋጋና እያስለቀቀ ደም በተቃባ ግንኙነት ባለቤት ሆኗል ብሎ ለማመን ያስቸግራል፡፡ ይህ ማለት ግን በማንኛውም ህዝብ እንደተለመደው በደም ግንኙነት ቅርበት በቅርብ ዝምድና በመመራት፣ በአንድ ኩታገጠም ቦታ መስፈርና በአለመግባባት ወቅት በደም ግንኙነት ቅርበትና በቅርብ ዝምድና ቡድን ተመስርቶ መጋጨትን መካድ አይሆንም፡፡ የሀዲያ ህዝብ በአፈ ታሪኩ የሚያስታውሳቸው የእርስ በርስ አለመግባባቶችና ግጭቶችም ቢሆኑ እንደማንኛው በወንድማማቾች መካከል በፍላጐትና በአስተሳሰብ ልዩነት ወይም በዉጭ ሀይሎች ግፊት ሊከሰት እንደሚችለውና በቀላሉ በሀዲያ ሴራ /Seera/ ሊፈቱ እንደሚችሉ ዓይነት መጠነኛ ግጭቶች የነበሩ ሲሆን ጦርነት በሚባል ደረጃ ሊገለጹ አይገባም፡፡

ይልቁንም ከላይ እንደተገለጸው በሀዲያ ጊቾዎች መካከል ነበረ የሚባለውን ጦርነቶችንና መገፋፋቶችን መሰረት ያደረገ ትንተና መረጃዎችን በጥንቃቄ ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ፣ ከሀዲያ ብሄር አጠቃላይ ማንነት ይልቅ ለሀዲያ ጊቾዎች ማንነትና ታሪክ ትኩረት በመስጠትና ልዩነቶችን በማጉላት የሀዲያን ህዝብ አንድነት የሚያንጸባረቅበትን ታሪክን፣ ቋንቋንና ባህልን የሚያደበዝዝ አዝማሚያ ያለው ይመስላል፡፡ በተለይም የአንዳንዶቹ የምርምር ሥራዎች ቢያንስ ቢያንስ መረጃ

የተሰበሰበበት ወቅት (ለምሳሌ፣ ከ1980 ዓ.ም. እንደ አውሮፖውያን አቆጣጠር በፊት) የሀዲያን ብሄር ማንነት የማጥፋት ወይም የማደብዘዝ የብዙ ዓመታት የተጠናከረ እንቅስቃሴ ቀጣይ ዘመን መሆን መቻሉ ትንተናዎቹ በዘመኑ ተጽእኖ ስር የወደቁ እንዳይሆኑ ጭምር ያስጋል፡፡

## 2.6. የሀዲያ ህዝብ ታሪክ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻዉ ሩብ እስከ 1974 ዓ.ም.

በኦሮሞ ህዝብ መስፋፋትና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች የቀድሞ ጥንካሬውን አጥቶ በጣም ውስን በሆነው በአሁኑ የሀዲያ አካባቢ ብቻ ማንነቱን አስጠብቆ የቀረው የሀዲያ ህዝብ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ የገጠመው ከፍተኛ ፈተና በንጉሥ ምኒልክ ሁለተኛው መሪነት የተደረገው የሸዋ ክርስቲያናዊ መንግሥት የወረራ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የሸዋ ክርስቲያናዊ መንግስት በንጉስ ምኒልክ ሁለተኛው ዘመን በሀዲያ ህዝብ ላይ የከፈተው የወረራና የበላይነትን የማረጋገጥ እንቅስቃሴ የሀዲያን እያንዳንዱ ጊቾ /Giichcho/ ለብቻው በማጥቃትና በማስገበር ከዚያም ወደሚቀጥለው በመሸጋገር ላይ የተመሰረተን ዘዴን ተከትሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሀዲያ አካባቢ የሚገኙ አንዳንድ ማህበረሰቦች /ለምሳሌ፣ከምባታና ጉራጌ/ ለክርስቲያኑ የሸዋ መንግሥት ይሰጡ የነበረው ድጋፍ ለወራሪ ሃይል ጥንካሬንና ለወረራውም መንደርደሪያ ቦታ ሰጥቶታል፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የወረራውን እንቅስቃሴ በአግባቡ ለመረዳት እያንዳንዱ የሀዲያ ጊቾ ከሸዋ ወራሪ ሃይል ጋር ያደረገውን ተገድሎ መቃኘት ተገቢ ይሆናል፡፡

የሸዋ ወራሪ ሀይል ወደ ደቡብ የዛሬው የኢትዮጵያ ክፍል ባደረገው የወረራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ የተቃውሞ ጠርነት ከገጠመው አካባቢዎች የቀቤና /Qabeena/ ሀዲያ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ ቀቤና በዛሬው የጉራጌ ዞን ምዕራባዊ ጫፍ ላይ





የሚገኝ አንዱ የሀዲያ ጊቾ /Giichcho/ ነው፡፡ በአብዛኞቹ ጸሀፊዎች አገላለጽ ሰሜን ሀዲያ ተብለው ይጠራሉ፡፡

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የቀቤናን ህዝብ በአግባቡ አደራጅተውና ማንነታቸውን ጠብቀው በጥንካሬ የያዙትን አካባቢ ተቆጣጥረው እንዲቆዩ ካስቻሉ ታላላቅ መሪዎች መካከል ዋልጋ ሞጬ / waalga moce/ የቀቤና ተዋቂ መሪና የሀሰን ኢንጀሞ አባት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በዋልጋ ሞጬ መሪነት ዘመን ለምሳሌ የቀቤና ሀዲያዎች የዜናበርን አካባቢ በቋምነት መኖሪያቸው አድርገው ሊይዙ ችለዋል፡፡ ይህ በቀቤና ሀዲያዎች ቋሚ መኖሪያ ተደርጐ የተያዘው የዜናበር አካባቢ በጣም ጠቃሚና እስትራተጂያዊ መሬት ሲሆን በምሥራቅ፣ ደቡብ ምሥራቅና ደቡብ አቅጣጫ በካሬብ ወንዝ እና በሰሜን አቅጣጫ በዋቤ ወንዝ የተከበበ ነው፡፡

እነዚህ ወንዞች ለቀቤና ሀዲያዎች እንደተፈጥሮ ምሽግ ሆነው ያገለግሉ ነበረ፡፡ በሁለቱ ትልልቅ ወንዞች የተከበበው የዜናበር አካባቢ በአካባቢው ባሉት ሌሎች የጉራጌ ህዝቦች ለምሳሌ የእክሊል ፣ የመቆርቆር፣ የወለኔ ህዝቦች የቀቤና ሀዲያዎች ሀገር ተደርጐ እውቅና የተሰጠው ቦታ ነው፡፡ በዚያ ዘመን የቀቤና ህዝብ የፖለቲካና የሃይማኖት ዋና መዕከል ሴባ / Seebba/ የሚባል ቦታ ነበረ፡፡

እንግዲህ እስልምና ወደሌሎች የጉራጌ አካባቢዎች መስፋፋት የቻለው ከዚህ የቀቤና አካባቢ በመነሳት መሆኑ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ቀቤናዎች ከሌሎች የአካባቢው የጉራጌ ህዝቦች ቀድመው እስልምናን የተቀበሉ በመሆናቸው ነው፡፡ የቀቤና ተዋቂ መሪ የነበሩት ዋልጋ ሞጬ ከሞቱ በኋላ እሳቸውን

ተከተው የቀቤናን አካባቢ የመሩት ኡመር በቅሳ /Umar Baqqisa/ የተባሉ የቸሃ ተወላጅ እስላም ናቸው። የኡመር በቅሳን መተካት ያመቻቹትና የቀቤናን ህዝብ ያሳመኑት አሊ ደነቦ /Aii Dannabo/ የተባሉ የቀቤና ተወላጅ የሆኑ የእስልምና ሃይማኖት መሪ ናቸው። ለኡመር በቅሳም ሃሰን ኤንጀሞ / Hasan Enjaamo/ አፈ-ጉባኤ ሆነው እንዲያገለግሉ በቀቤና ህዝብ ተመድበዋል።

የኡመር በቅሳ ዘመን በቀቤና አካባቢ እስልምና በጣም የተጠናከረበት ዘመን ሲሆን እንደ ሼህ ዋራቆ /Waaraaqo/ ከይፋት፣ ሼህ ኡመር ዲሎ /Umar Diilo/ ከአፋር በመምጣት የእስልምና ትምህርት ያስፋፉበት ዘመን ነበር። እንግዲህ ንጉስ ምኒልክ II የመጀመሪያውን የቀቤና ዘመቻ ያካሄዱት በኡመር በቅሳ የመሪነት ዘመን ነበር። ይህ የመጀመሪያው ዘመቻ የተካሄደው በ1875 ዓ.ም. ሲሆን የቀቤና መሪ የነበሩትና የቸሃ ተወላጅ የነበሩት ኡመር በቅሳ በሰላም ለንጉስ ምኒልክ ወራሪ ሃይል እጃቸውን በመስጠት ገብተዋል። በዚህም ምክንያት ቀቤና በምኒልክ ቁጥጥር ስር ሲወድቅ ኡመር በቅሳ የግራዝማችነት ማዕረግ ከምኒልክ ተሰጥቷቸው ግራዝማች ኡመር ሊባሉ ችለዋል።

ኡመር በቅሳ በቀቤና ህዝብ ላይ ያሳረፉት በጣም ጨቋኝ የሆነ አስተዳደርና ለክርስቲያኑ መንግስት በሰላም ገብተው የክርስቲያኑን መንግስት ማእረግ መቀበላቸው የቀቤና ህዲያዎች በኡመር በቅሳ አመራር ላይ የነበራቸው ትዕግሥት ተሟጦ እንዲያልቅ አድርጓል። ይህ ሁኔታ ህዲያ ባልሆነ መሪ አንመራም ወደሚል የቀቤና እንቅስቃሴ በማምራቱ ከ33 ዓመታት በኋላ የኡመር በቅሳ መሪነት አብቅቶ ሀሰን ኤንጃሞ በቦታው ሊተካ ችሏል።





ሀሰንና ኤንጃሞ ሁለቱም የአንድ ግለሰብ የተለያዩ ስሞች ሲሆኑ ሀሰን የእስልምና ሃይማኖት ስም ሲሆን ኤንጃሞ ደግሞ ቤተሰብ ያወጣለት ስም ነው። በእስልምና ስሙ ሀሰን ኤንጃሞ፣ ሰይድ ሀሰን ተብሎ ይጠራል። ሀሰን ኤንጃሞ ወደ ቀቤና ህዝብ መሪነት እንዲመጣ በአካባቢ ያሉና የክርስቲያኑን መንግስት የበላይነት የሚቃወም ህዝቦች ለምሳሌ፣ የወለኔ ህዝብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በተለይም የወለኔ መንፈሳዊ አባትና የቀድሞ የሀሰን ኤንጃሞ የሀይማኖት አስተማሪ የሆኑት ሼክ አብዱል አዚዝ የሀሰን ኤንጃሞን አጠቃላይ አስተሳሰብ በከፍተኛ ሁኔታ የቀረጹ ግለሰብ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ከቀቤና ህዝብ በአጠቃላይና ከሀሰን ኤንጃሞ ጋር በተለይ ጠንካራ ግንኙነት የነበራቸው የወሎ ሙስሊም ሰፋሪዎችና የይፋት የእስልምና አስተማሪዎች የራሳቸውን ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ አሳርፈዋል። የጅማ እስላማዊ መንግሥት መሪ የነበሩት አባጅፋር ሀሰን ኤንጃሞንና የቀቤናን ህዝብ በማገዝ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጠንካራ ተቃውሞ እንዲቀሰቀስ የበኩላቸውን አስተዋዕኦ አበርክተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ምንጮች ለምሳሌ (ባሀሩ፡ 2005a: 61)˚ በሀሰን ኤንጃሞ የተመራው የቀቤናዎች የአመፅ እንቅስቃሴ ከሱዳኑ የመህዲስት እንቅስቃሴ ጋር ከነበረዉ የግንኙነት እድል የራሱን የሆነ ትምህርት መውሰዱንና መነቃቃት ማግኘቱን ይጠቅሳሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን አጠቃላይ ሁኔታዎች በመጠቀም የሸዋን ወራሪ ሀይል ለመቋቋም እንዲቻል ሀሰን ኤንጃሞ ኡመር በቅሳን ከስልጣን ለማውረድ የራሱን ደጋፊዎችና የቀቤናን ሕዝብ በሴባ በማደራጀት እንቅስቃሴ ጀመሩ። የዚህ ዉጤት በሆነዉ የግልበጣ እንቅስቃሴ ኡመር በቅሳ ተሸንፈው

ወደ አክሊል ሊሸሹ ችለዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የቀቤና ሀዲያዎች መሪ ሀሰን ኤንጃሞ በመሆን በአካባቢው አጠቃላይ ጅሃድ አውጀዋል፡፡ ሀሰን ኤንጃሞና ደጋፊዎቹ የመጀመሪያውን የእስልምና ሃይማኖትን የማስፋፋት እንቅስቃሴ ያካሄዱት በአካባቢ ባሉት እስልምናን ባልተቀበሉ ጉራጌዎች ላይ ሲሆን፣ ይህ እንቅስቃሴ በቀላሉ ውጤታማ ሊሆን ችሏል፡፡

በመቀጠልም ሀሰን ኤንጃሞ ጠንካራ የቀቤናን የጦር ሃይል ካደራጀ በኋላ በምኒልክ II ወራሪ ሃይል ላይ ጦርነት አውጀዋል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የተጀመረው በ1885 ዓ.ም. የሶዶ ጉራጌ ገዥ ከሆነው ከደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ ጋር ሀሰን ኤንጃሞ ባደረገው ጦርነት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሀሰን ኤንጃሞ የቀቤና ሀይሎችና በሚኒልክ ወራሪ ሠራዊት መካከል እስከ 1889 ዓ.ም. ድረስ የዘለቀ ጦርነት ተካሃዷል፡፡

በሁሉቱም ሀይሎች መካከል ከተደረጉት ጦርነቶች መካከል በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ በ1888 ዓ.ም. ምኒልክ በደጃዝማች ወልዴ አሻግሬ መሪነት ወደ ሀሰን ኤንጃሞ አገር /ቀቤና/ ያደረጉት ጦርነት ይገኛል፡፡ ለዚህ ጦርነት ሀሰን ኤንጃሞ ሠራዊቱን በመያዝ ወደ ወሰኔ በመሄድ አፈረር / Afarar/ በሚባል ቦታ ላይ ሠፍሯል፡፡ ሀሰን ኤንጃሞ አፈራር ላይ ለጦርነት ሲዘጋጅ ከንጉስ ምኒልክ ሁለተኛ የንጉሱን የበላይነት ተቀብሎ ሀሰን ኤንጃሞ እንዲገባ መልእክት ተልኮለታል፡፡ ለዚህም የንጉሡ መልእክት እሽታውን ከገለጠ፣ ለሀሰን ኤንጃሞ የራስነት ማዕረግ እንደሚሰጠውና ከአዋሽ በስተ ደቡብ ያለውን አገር በአጠቃላይ እስከ ከምባታ ድረስ ገዥ አድርገው እንደሚሾሙት ቃል ገብተዋል፡፡





ነገር ግን ሀሰን ኤንጃሞ ይህንን የንጉሡን ስጦታ ከአንድ እስልምናን ከማያውቅ ከሃዲ ጋር አልደረደርም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህ አሰመግባባት ወደ ዊልንቆ /Wilinqo/ ጦርነት እንዲገቡ አድርጓል፡፡ በዊልንቆ ጦርነት እንቢታውን የገለፀው ሀሰን ኤንጃሞ በምኒልክ ወራሪ ሃይሎች ላይ አሸናፊ መሆን ችሏል፡፡

ከዚህ በኋላ በምኒልክ ሃይሎችና በቀቤናው የሀሰን ኤንጃሞ ሀይሎች መካከል የመጨረሻ ጦርነት የተካሄደው 1889 ዓ.ም. በጀብዱ ላይ ነው፡፡ በዚህ ጦርነት የክርስቲያኑ ወራሪ መንግስት ሃይሎች በፊታውራሪ ሃብቴ ጊዮርጊስና በራስ ጉበና ዳጩ ተመርተዋል፡፡ በእስላሞች በኩል ከተለያዩ የሀዲያና የጉራጌ አካባቢዎች የተወጣጡ ሀይሎች በተለያዩ የጦር መሪዎች የተመሩ ሲሆን የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ግን ሀሰን ኤንጃሞ ነበረ፡፡

በጀብዱ ሜዳ ጦርነት በሀሰን ኤንጃሞ የሚመሩት የእስላም ሃይሎች የተሸነፉ ሲሆን ሀሰን ኤንጃሞም ወደ ጅማ ተሰዷል፡፡

የጦርነቱን ሁኔታ ከበሞ (2007: 57) አለቃ አጥሜን በመጥቀስ እንደሚከተሰዉ ጽፏል፡፡

> *ጎበና ወዲያዉ ዘምተዉ ነበረ ወደ ቀቤና፣በመጋቢት 18/81 ዓ. ም እ. ኢ. አ. ቀቤናን ቸሃን ስልጤን የእስላምን አገር ሁሉ አጠፉት፣መሬቱን እየከፋፈሉ ላማራ ሰጡት፣ ኡመር በክሳን ያዙት፣እንጃሞ ወደ ጂማ ሸሸ፣አገሩን ይዘዉ ሰራዊትዎን በዚያዉ ሾመዉ አደላድለዉ በሰኔ ወር እንጦጦ ገቡ፡፡*

ሀሰን ኤንጃሞ ወደ ጂማ የተሰደደበት መሠረታዊ ምክንያት ከአባጅፋር ወታደራዊ ድጋፍ በማግኘት እንደገና ተመልሶ ከወራሪው ሀይል ጋር ለመዋጋት ቢሆንም የጠበቀውን ድጋፍ ማግኘት ተስኖታል። ይልቁንስ አባጅፋር ከሀሰን ኤንጃሞ ጋር ወደ ጂማ አብረው ለተሰደዱት ሀዲያዎች ቁምቢ /Qumbii/ በሚባል ቦታ መሬት በመስጠት እንዲሰፍሩ ፈቅደዋል። የጦርነቱ ሁኔታ ከተረጋጋ በኋላ ሀሰን ኤንጃሞ ወደ አገሩ ወደ ቀቤና በመመለስ ጉዞ ላይ እያሰ በወባ ትንኝ ተነድፎ በቀቤና ሴባ በሚባለው ማዕከሉ ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

የምኒልክ ሠራዊት በሀሰን ኤንጃሞ ላይ የተቀዳጀው ድል በአካባቢው አጠቃላይ ማህበረሰብ ላይ የተገኘ ድል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በተሰይም በቀቤናና በጉራጌ እስላሞች ላይ በአጠቃላይ የሚኒልክ ሠራዊት የበላይነት ሊቀዳጅ ችሏል። ይህ ተመሳሳይ ድል የምኒልክ ሠራዊትና መሪዎች የተቀረውን የሀዲያ ህዝብ ለማስገበር በር የከፈተ አጋጣሚ ሊሆን ሲችል በዛሬው የሀዲያ አካባቢ ያሉት ህዝቦችም የተቃውሞ ስሜት በእጅጉ የጐዳ ሆኗል። በመሆኑም ሀሰን ኤንጃሞንና የቀቤናን ሀዲያዎች ብቻ ከማሸነፍ ያለፈ ትርጉም ያለውን ሁኔታ ሊፈጥር ችሏል።

የምኒልክ ወራሪ ሃይል ከቀቤና ውጪ ያሉትን የሀዲያ አካባቢዎችንም የማስገበር የጦርነት እንቅስቃሴ የጀመረው የሶዶ ጉራጌዎችን በቁጥጥር ሥር ካደረገና ደጃዝማች ወልዴ አሻግሬን የአካባቢው ገዥ አድርጎ ከሾመ በኋላ በ1878 ዓ.ም. አካባቢ ነው። ከዚህ አንፃር የሶዶ ጉራጌዎችን በሸዋ መንግሥት ክልል ውስጥ ካስገቡ በኋላ የምኒልክ ሀይሎች በቀጥታ ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ሊብዶ /ማረቆ/ ሀዲያዎች ነው። ኤደሞ (1999) እንደገለፀው የልብዶ ህዝብ በርካታ





ተከታታይ ጦርነቶችን ከምኒልክ ተስፋፊ ሃይሎች ጋር በቀጥታና ከአካባቢው የተስፋፊ ሃይሎች ደጋፊዎች ጋር እንዲሁ በተዘዋዋሪ አካሂዷል።

ነገር ግን፣ በተሰይም የምኒልክ ወራሪ ሠራዊት ከገጠመው ጠንካራ ተቃውሞ፣ በሊብዶ ህዝብና በወራሪው ሠራዊትም ላይ ከደረሰዉ ከፍተኛ ከሆነ እልቂትና ጥፋት አንፃር ከሊብዶ ህዝብ ህሊና የማይጠፉ ሁለት ዋና ዋና ጦርነቶች እንደሚገኙ ኤደሞ (1999)። እነዚም ጦርነቶች በሊብዶ ህዝብ ዘንድ የአጃቾና /Ajaachcho/ የለጩቦ /Laccabo/ ጦርነቶች ተብለው ይጠራሉ። የጦርነቶቹ መጠሪያም ከሊብዶ ህዝብ ጦር መሪዎች ስም የተወሰደ ነው።

ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ጦርነቶች የመጀመሪያው የአጃቾ ጦርነት ሲሆን የጦሩ መሪም አጃቾ ተብሎ ይጠራ ነበር። በዚህ ጦርነት የሊብዶ ህዝብ የምኒልክን ተስፋፊ ሃይል አሸንፎ ሊመልስ ችሏል። የአጃቾ ጦርነት የተካሄደበትን ትክክለኛ ዘመን ግን ማወቅ ባይቻልም ተስፋዬ (1993: 450) ሴኪን በመጥቀስ ስለ ጦርነቱ የሚከተሰዉን ጽፏል።

> *ማረቆዎች ልዩ የሆነ ቋንቋ ይናገራሉ፣ በዝርፊያ የሚኖሩና ጥሩ የሆኑ ፈረሶች ያሏቸዉ ናቸዉ።... ምኒልክ ጦር በከፈተባቸዉ ጊዜ የጦር መሳሪያዉን አልፈሩም።የፈረሶቻቸዉን ጆሮ በጨርቅ በመሸፈን ጠላታቸዉን የምኒልክን ሰራዊት ፊት ለፊት ገጠሙት።አንድ የጥይት ድምጽ ከ2000-3000 ህዝብ ሊያስበረግግ በሚችልበት አገር እንዲህ ማድረጋቸዉ ለታላቅ ጀግንነታቸው ጥሩ ምስክር ነዉ። የማረቆ ነገድ ከ7000 ግለሰቦች የማይበልጥ ነዉ። ዳር ድንበሩ ከእንግድህ ወዲያ በመንዝና በአሩሲ አይገፋም፣ወደፊት ሊደርስ ከሚችለዉ ጥቃት ተጠብቋል።*